የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፲፭
አዲስ አበባ መጋቢት ፱ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

28th Year No. 15
ADDIS ABABA 18th March, 2022

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፷፯/፪ሺ፲፬
የመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ........ገጽ፲፬ሺ፲፫

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፷፯/፪ሺ፲፬

## ስለ መንግሥት ሠራተኞች ጡረታ ለመደንገግ የወጣ አዋጅ

የማኅበራዊ መድን ሥርዓትን በማስፋፋት ደረጃ በደረጃ ለዜጎች እንዲዳረስ ማድረግ ከሀገሪቷ ማኅበራዊ ጥበቃ ፖሊሲ አንዱ አካል በመሆኑ፤

የሥርዓቱ ተጠናክሮ መቀጠል ለማኅበራዊ ፍትሕ፣ ለኢንዱስትሪ ሰላም፣ ለድህነት ቅነሳ፣ ለምርታማነትና ለልማት ጉልህ አስተዋጽኦ ስለሚኖረው፤

በሥራ ላይ ያለውን የመንግሥት አገልግሎት የጡረታ ዐቅድ አቅም በፈቀደ መጠን ማጠናከር፣ አዋጆቹን በማሻሻል ማጠቃለልና ለሥራው አፈጻጸም ምቹ ሁኔታ መፍጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ ፈንድን ቀጣይነትና አስተማማኝነት ማረጋገጥ፣ ፈንዱን በኢንቨስትመንት ማዳበርና ግልጽ የሆነ የአስተዳደር ሥርዓት እንዲኖረው ማድረግ በማስፈለጉ፤

## Content

Proclamation No.1267/2022
Public Servants' Pension Proclamation ................................................Page 14013

## PROCLAMATION No. 1267/2022

## A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR PUBLIC SERVANTS' PENSION

**WHEREAS**, it is part of the country's social protection policy to expand social insurance system and reach citizens step by step;

**WHEREAS**, the strengthening and sustainability of the system greatly contributes to social justice, industrial peace, poverty reduction, productivity and development;

**WHEREAS**, it has been found necessary to strengthen, to the extent circumstances allow, the public service's pension scheme by revising and consolidating the existing laws to create suitable condition for implementation process;

**WHEREAS**, it has been necessary to ensure the sustainability and reliability of the public servant's pension fund through investment requires transparent governance system;

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁጥር ፲፪ሺ፷፯/፪ሺ፲፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩/ "የመንግሥት ሠራተኛ" ማለት በመንግሥት መሥሪያ ቤት፣ በመንግሥት የልማት ድርጅት ወይም በመንግሥት በሚካሄድ ፕሮጀክት ወይም ፕሮግራም በቋሚነት ወይም ለተወሰነ ጊዜ ወይም ለተወሰነ ሥራ በመቀጠር በየወሩ ደመወዝ እየተከፈለው የሚሠራ ሰው ሲሆን የመንግስት ተሿሚዎችን፣ የምክር ቤት አባላትን፣ ዳኞችን፣ ዐቃቢያነ ሕግን፣ የመከላከያ ሠራዊትን እና የፖሊስ አባላትን ይጨምራል፤

፪/ "የመንግሥት አገልግሎት" ማለት በመንግሥት ሠራተኛው በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፮) በተመለከቱ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የተፈጸመ አገልግሎት ነው፤

፫/ "ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊ" ማለት ሚኒስትር፣ ሚኒስትር ዴኤታ፣ ምክትል ሚኒስትር ወይም ተመሳሳይ ደረጃ ያለው የመንግስት ኃላፊ ነው፤

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows.

## PART ONE

## GENERAL

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Public Servants' Pension Proclamation No. 1267/2022".

### 2. Definition

In this Proclamation, unless the context otherwise requires:

1/ "Public ervant" means monthly salaried person employed permanently or for definite period or piece of work in a public office, public enterprise or project or program carried out by government, and includes government appointees, members of parliament, Judges. Public Prosecutors, members of the defense force and the police;

2/ "Public service" means service rendered by public servants in public offices stipulated under Sub Article (6) of this Article;

3/ "Senior government official" means Minister, Minister of State, Deputy Minister or any government official having an equivalent rank;

፬/ “የምክር ቤት አባል” ማለት አፈጉባዔ፣ ምክትል አፈጉባዔ፣ ማንኛውንም የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባልን እና በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት የፌደሬሽን ምክር ቤት በቋሚነት የሚሰራ የፌደሬሽን ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴ አባልን ያጠቃልላል፤

፭/ “አፈጉባዔ” ወይም “ምክትል አፈጉባዔ” ማለት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ወይም የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈጉባዔ ወይም ምክትል አፈጉባዔ ነው፤

፮/ “የመንግሥት መሥሪያ ቤት” ማለት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በመንግሥት በጀት የሚተዳደር መሥሪያ ቤት፣ ተቋም ወይም አካል ሲሆን በራሳቸው ገቢ የሚተዳደሩ መንግሥታዊ ተቋማትና የልማት ድርጅቶችን ይጨምራል፤

፯/ “መንግሥት” ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል መንግሥት እና የክልል መንግሥታትን ያጠቃልላል፤

፰/ “ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፵፯ ንዑስ-አንቀጽ ፩ የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን በንዑስ-አንቀጽ ፪ የተቋቋሙትን ሌሎች ክልሎች እንዲሁም የአዲስ አበባና የድሬደዋ ከተሞች አስተዳደሮችን ይጨምራል፤

፱/ “የመከላከያ ሠራዊት አባል” ማለት በሀገር መከላከያ ሠራዊት ውስጥ በመከላከያ ሠራዊት መተዳደሪያ ሕጎች መሠረት ተቀጥሮ ወታደራዊ አገልግሎት የሚሰጥ ማንኛውም ሰው ነው፤

4/ “Member of parliament” means Speaker, Deputy speaker, includes any member of the House of Peoples’ Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and member of the House of Federation working permanently in the standing committees of the House of Federation;

5/ “Speaker” or “Deputy speaker” means the speaker or Deputy speaker of the House of Peoples’ Representatives or the House of the Federation;

6/ “Public office” means any government office, institution or organ wholly or partly run by government budget, and includes public institutions and enterprises run by their own income;

7/ “Government” mean the federal government and includes the regional states of the Federal Democratic Republic of Ethiopia;

8/ “Region” means any region referred to in Article 47(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, other regions estabilished as of Article 47(2) of Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and includes the Addis Ababa and Dire Dawa city administrations;

9/ “Member of the defense force” means a person permanently employed in the National Defense Force to render military service in accordance with laws regulating the administration of the Defense Force;

፲/ "የፖሊስ አባል" ማለት በፌዴራል ወይም በክልል መንግሥት በፖሊስ መተዳደሪያ ሕጎች መሠረት ተቀጥሮ አገልግሎት የሚሰጥ ማንኛውም ሰው ሲሆን የወህኒ (የማረሚያ ቤት) ፖሊስን ይጨምራል፤

፲፩/ "ሲቪል መንግሥታዊ አገልግሎት" ማለት ከመከላከያ ሠራዊት እና ከፖሊስ አባልነት ውጪ በሌሎች የመንግሥት ሠራተኞች የሚፈጸም አገልግሎት ነው፤

፲፪/ "ወታደራዊ አገልግሎት" ማለት በሀገር መከላከያ ሠራዊት አባላት የሚፈጸም አገልግሎት ነው፤

፲፫/ "የፖሊስ አገልግሎት" ማለት በፖሊስ አባላት የሚፈጸም አገልግሎት ሲሆን የማረሚያ ቤት ፖሊስ አገልግሎትንም ይጨምራል፤

፲፬/ "የልማት ድርጅት" ማለት የመንግሥት የልማት ድርጅቶችንና ከ፶ በመቶ ያላነሰ የካፒታል ድርሻ የመንግሥት የሆነባቸውን ድርጅቶችን ያጠቃልላል፤

፲፭/ "አበል" ማለት የአገልግሎት ጡረታ አበል፣ የጤና ጉድለት ጡረታ አበል፣ የጉዳት ጡረታ አበል ወይም የተተኪዎች ጡረታ አበል ሲሆን የዳረጎት አበልን ይጨምራል፤

፲፮/ "ደመወዝ" ማለት ለሥራ ግብር እና ለማንኛውም ሌላ ጉዳይ ተቀናሽ የሚሆነው ሂሳብ ሳይነሳለት አንድ ሠራተኛ በመደበኛ የሥራ ሰዓት ለሚሰጠው አገልግሎት የሚከፈለው ሙሉ የወር ደመወዝ ነው፤

፲፯/ "ባለመብት" ማለት በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት አበል የሚያገኝ ወይም አበል ለማግኘት የሚያስፈልጉትን ሁኔታዎች የሚያሟላ ሠራተኛ ወይም ተተኪ ነው፤

10/ "Member of the police" means a person permanently employed and renders service in federal or regional police including prison police in accordance with laws governing the administration of police;

11/ "Civil service" mean service rendered by public servants other than members of the Defense Force and the Police;

12/ "Military service" means service rendered by members of the National Defense Force;

13/ "Police service" means service rendered by members of the Police and includes prison police service ;

14/ "Enterprise" include public enterprises and enterprises in which the government's capital share is not less than 50%;

15/ "Benefit" means retirement pension, invalidity pension, incapacity pension or survivors pension and includes gratuity;

16/ "Salary" means the monthly salary received by a public servant, for services rendered during regular working hours, without the deduction of any amounts in respect of income tax and any other matter;

17/ "Beneficiary" means a public servant or his survivor who receives benefits or fulfils the conditions for receiving benefits in accordance with this Proclamation;

፲፰/ "ተተኪ" ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵(፫) የተዘረዘሩትን ያጠቃልላል፤

18/ "Survivor" include persons referred to under Article 40(3) of this Proclamation;

፲፱/ "የመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ ዐቅድ" ማለት በዚህ አዋጅ ለሚሸፈኑ የመንግሥት ሠራተኞች የጡረታ አበል ክፍያ ለመስጠት የተቋቋመ ሥርዓት ነው፤

19/ "Public Servants Pension Scheme" means a system established to pay pension benefits to public servants covered under this Proclamation;

፳/ "የጡረታ ፈንዶች" ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የሚሰበሰብ የጡረታ መዋጮና ለሚፈጸም የአበል ክፍያ ተግባር የተቋቋሙ የመንግሥት ሠራተኞች የጡረታ ፈንዶች ናቸው፤

20/ "Pensions funds" means Public Servants Pension Funds established for the purposes of collecting pension contributions and effecting payments of benefits pursuant to this Proclamation;

፳፩/ "ለተወሰነ ጊዜ ወይም ለተወሰነ ሥራ" ማለት በመንግሥት መሥሪያ ቤት፣ በመንግሥት የልማት ድርጅት ወይም በመንግሥት በሚካሄድ ፕሮጀክት ወይም ፕሮግራም ውስጥ በጊዜያዊነት ወይም ለቁርጥ ሥራ ከ፷ ቀናት ላላነሰ ጊዜ በመቀጠር በየወሩ ደመወዝ እየተከፈለበት የሚከናወን ሥራ ሲሆን በቀን ሥራ፣ በጥጥ ለቀማ፣ በሸንኮራ አገዳ ቆረጣ እና ሌሎች መሰል በየዓመቱ እየተደጋገሙ የሚከናወኑ ሥራዎችን አይጨምርም፤

21/ "Definite period or piece of work' means a work in a public office, public enterprises or project or program undertaken by government on the bases of temporary or piece of work employment for not less than 60 days and it does not include a work to be performed by daily laborer, a work for cotton collection, sugar cane cutting and such other similar works regularly repeated in the course of the year;

፳፪/ "አግባብነት ያለው የመንግሥት አካል" ማለት በሕግ ብሔራዊ መለያ ቁጥር ለመስጠት ሥልጣን የተሰጠው አካል ነው፤

22/ "Relevant government body" means a body legally authorized to issue national identification number,

፳፫/ "አስተዳደር" ማለት የመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ ፈንድን ለማስተዳደር በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ የሚቋቋም የመንግሥት ሠራተኞች ማኅበራዊ ዋስትና ፈንድ አስተዳደር ነው፤

23/ "Administration" means the Public Servants Social Security Fund Administration to be established by Council of Ministers Regulation;

፳፬/ "ተቆጣጣሪ ባለስልጣን ማለት" የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ነው፤

24/ "Supervisory authority "means National Bank of Ethiopia;

፳፭/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፳፮/ በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴትንም ያካትታል፡፡

## ፫/ የተፈጻሚነት ወሰን

፩/ የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑ የውጭ ዜጎችን የጡረታ ጥቅም የሚመለከተው የአዋጅ ቁጥር ፪፻፸/፲፱፻፺፬ ድንጋጌ እና ሀገሪቷ ተዋዋይ ወገን የሆነችባቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ይህ አዋጅ በዜግነት ኢትዮጵያዊ ለሆኑ የመንግሥት ሠራተኞች ተፈጻሚ ይሆናል፤

፪/ የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፪(፮) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በአዋጅ ቁጥር ፮፻፶፫/፪ሺ፩ አንቀጽ ፶፬ መሠረት መብቶቻቸውንና ጥቅሞቻቸውን እንዲያጡ የተደረጉ ከፍተኛ የመንግስት ኃላፊዎችንና የምክር ቤት አባላትን በሚመለከት የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፱(፭)፣ አንቀጽ ፳(፪)፣ አንቀጽ ፳፩(፪)፣ አንቀጽ ፳፪(፫) እና አንቀፅ ፳፫(፪) ተፈጻሚ አይሆኑም፡፡

## ክፍል ሁለት

## ስለማኅበራዊ ዋስትና ምዝገባና መለያ ቁጥር

### ፬. ምዝገባ

፩/ ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት መሥሪያ ቤቱ የተቋቋመበትን ሕግ፣ የመንግሥት ሠራተኛው ለመጀመሪያ ጊዜ ሲቀጠር የሞላውን የሕይወት ታሪክ ፎርም፣ የተሰጠውን የቅጥር ደብዳቤ እና ሌሎች በአስተዳደሩ የሚወሰኑ መረጃዎችን ለምዝገባ ለአስተዳደሩ ማቅረብ አለበት፡፡

25/ "person" means any natural or juridical person;

26/ any expression in the masculine gender includes the feminine.

## 3. Scope of Application

1/ Without prejudice to the appropriate provisions of Proclamation No. 270/2002 that provide pension coverage to foreign nationals of Ethiopian origin, and international treaties to which the Country is a party, this Proclamation shall be applicable to public servants who are Ethiopian nationals;

2/ Without prejudice to the provision of Article 52(6) of this Proclamation, the provision of Article 19(5), Article 20(2), Article 21(2), Article 22(3) and Article 23(2) of this Proclamation shall not be applicable with respect to senior government officials and members of parliament who have been deprived of their rights and benefits pursuant to Article 54 of Proclamation No. 653/2009.

## PART TWO

## SOCIAL SECURITY REGISTRATION AND IDENTIFICATION NUMBER

### 4. Registration

1/ Any public office shall, for the purpose of registration, submit to the Administration copies of its establishment legislation, personal data of the public servant taken at the time of first employment, letter of employment issued to the public servant and other data determined by the Administration.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) መሠረት የሚቀርቡ የምዝገባ መረጃዎች፡-

ሀ) ነባር የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችንና የመንግሥት ሠራተኞችን የሚመለከቱ ሲሆን በአስተዳደሩ በሚወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ፤

ለ) ይህ አዋጅ ከጸናበት ቀን በኋላ የተቋቋመ የመንግሥት መሥሪያ ቤትን ወይም የተቀጠረ የመንግሥት ሠራተኛን የሚመለከት ሲሆን መሥሪያ ቤቱ በተቋቋመ ወይም ሠራተኛው በተቀጠረ በ፷ ቀናት ውስጥ መቅረብ አለባቸው፡፡

## ፭. የማሕበራዊ ዋስትና መለያ ቁጥር

፩/ ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም የመንግሥት ሠራተኛ ማስረጃ ተሟልቶ ሲቀርብ የማኅበራዊ ዋስትና መለያ ቁጥር ይሰጠዋል፡፡ ሆኖም የመንግስት ሠራተኛው በሌላ አግባብነት ያለው የመንግሥት አካል የሚሰጥ ብሔራዊ መለያ ቁጥር ካለው ይኸው ቁጥር የማኅበራዊ ዋስትና መለያ ቁጥር ሆኖ እንዲያገለግል ሊደረግ ይችላል፡፡

፪/ ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ ወደሌላ የመንግስት መሥሪያ ቤት ሲዛወር ወይም በሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም በጡረታ ዐቅድ በተሸፈነ የግል ድርጅት ሲቀጠር የማሕበራዊ ዋስትና መለያ ቁጥሩን ለተዛወረበት ወይም ለተቀጠረበት የመንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም የግል ድርጅት የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡

2/ The time limit for submission of data in accordance with Sub-Article (1) of this Article shall:

a) in the case of existing public offices and public servants, be determined by the Administration;

b) in the case of public offices established, or public servants employed after the effective date of this Proclamation, 60 days from the date of establishment or employment.

## 5. Social Security Identification Number

1/ Any public office or public servant shall, upon submission of completed data for registration, be assigned with social security identification number provided, however, that the public servant if any has been given the national identification number by the concerned government body, it may be taken as social security identification number.

2/ Any public servant, when transferred to another public office or employed by another public office or any private organization covered by pension scheme, shall notify his identification number to such office or organization.

## ፮. የምዝገባ መረጃ ለውጥን ስለማሳወቅ

፩/ ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት የራሱንና የመንግሥት ሠራተኛውን የምዝገባ መረጃ የሚመለከት ለውጥ ሲያጋጥም ለውጡ ከተከሰተበት ቀን ጀምሮ በ፷ ቀናት ውስጥ የተከሰተውን ለውጥ ከደጋፊ ማስረጃ ጋር አያይዞ ለአስተዳደሩ በማቅረብ ማሳወቅ አለበት፡፡

፪/ እያንዳንዱ የመንግሥት ሠራተኛ የቤተሰብ ሁኔታን የሚመለከት የመረጃ ለውጥ ሲያጋጥመው ከደጋፊ ማስረጃ ጋር ለሚሠራበት የመንግሥት መስሪያ ቤት በማቅረብ ማሳወቅ አለበት፡፡

፫/ አበል በመቀበል ላይ የሚገኝ ባለመብት በምዝገባ መረጃው ላይ ለውጥ ሲያጋጥመው ለውጡ ከተከሰተበት ቀን ጀምሮ በ፷ ቀናት ውስጥ ከደጋፊ ማስረጃ ጋር ለአስተዳደሩ በማቅረብ ማሳወቅ አለበት፡፡

፬/ ማንኛውንም የመንግሥት መሥሪያ ቤት፣ የመንግሥት ሠራተኛ ወይም የጡረታ ባለመብትን የሚመለከት የምዝገባ መረጃ ለውጥ ማሳወቂያ ሲቀርብ የማኅበራዊ ዋስትና የምዝገባ መለያ ቁጥር መጠቀስ አለበት፡፡

፭/ የማኅበራዊ ዋስትና የምዝገባ መለያ ቁጥር የተሰጠው የመንግሥት መሥሪያ ቤት በመፍረሱ በመከፋፈሉ ወይም በመቀላቀሉ ምክንያት ሠራተኞቹን እንዲረከብ የተደረገው የመንግሥት መሥሪያ ቤት በ፷ ቀናት ውስጥ ይህንኑ ለአስተዳደሩ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

## 6. Notification of Changes in Entries of Registration

1/ Any public office shall, when any change occurs in the entries of its social security registration or that of its public servant, notify such change to the Administration, with supporting evidence, within 60 days of the occurrence of such change.

2/ Every public servant shall notify, with supporting evidence, to the public office that he is working for, any change regarding his family status.

3/ Any beneficiary who is receiving benefits shall notify, with supporting evidence, to the Administration any change in the entries of social security registration within 60 days of the occurrence of such change.

4/ Any notification of change in the entry of social security registration relating to a public office, public servant or beneficiary, shall indicate the corresponding social security identification number.

5/ Any public office to which public servants are transferred following the dissolution, division or merger of another public office shall notify same, in writing, to the Administration within 60 days of the takeover.

፮/ የማኅበራዊ ዋስትና የምዝገባ መለያ ቁጥር የተሰጠው የመንግሥት የልማት ድርጅት ወደ ግል ይዞታ ሲዛወር ዝውውሩን ያስፈጸመው መንግስታዊ አካል በ፷ ቀናት ውስጥ ይህንኑ ለአስተዳደሩ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

፯/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፬(፩) እና አንቀጽ ፮ ንዑስ-አንቀጽ (፩)፣ (፪) እና (፫) የተደነገጉት ቢኖሩም በቅድሚያ የተመዘገበውን ዕድሜ ወይም የልደት ዘመን ለመቀየር ወይም ለማሻሻል የሚቀርብ ማንኛውም ማስረጃ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

፯. **የምዝገባ መረጃን አለማቅረብ የሚያስከትለው ውጤት**

፩/ በዚህ ክፍል በተመለከተው መሠረት የምዝገባ መረጃዎችን አደራጅቶ የማይዝና በወቅቱ ለአስተዳደሩ የማያስተላልፍ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የሚመለከተው ኃላፊ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፪ መሠረት ይቀጣል፡፡

፪/ በዚህ ክፍል በተመለከተው መሰረት የመረጃ ለውጥን በወቅቱ ለማያቀርብ የመንግሥት ሠራተኛ ወይም ባለመብት ለተተኪዎቹ የሚወሰነው አበል አስቀድሞ በአስተዳደሩ ተደራጅቶ በተያዘው መረጃ መሠረት ይሆናል፡፡

## ክፍል ሦስት

## ስለጡረታ ዐቅድ፣ ፈንዶችና መዋጮዎች

፰. **ስለመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ ዐቅድ መቋቋም**

የመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ ዐቅድ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

6/ Where a public enterprise is privatized, the government organ in charge of effecting the transaction shall notify in writing same to the Administration within 60 days.

7/ Notwithstanding Article 4(1) of this Proclamation and Sub-Articles (1), (2) and (3) of Article 6 any contrary evidence/ document brought to amend or change date of birth (age) registered at initial employment shall not be accepted.

7. **Effects of Failure to Submit Data for Registration effect**

1/ The concerned officer of a public office who fails to organize, keep and timely submit to the Administration data for registration as required under this Part shall be punishable in accordance with Article 62 of this Proclamation.

2/ Where a public servant or beneficiary fails to timely submit data relating to changes in entries of registration as required under this Part, his survivors' entitlements to benefits shall be based on the data that have already been organized and kept by the Administration.

## PART THREE

## PENSION SCHEME, FUNDS AND CONTRIBUTIONS

8. **Establishment of Public Servants Pension Scheme**

The Public Servants Pension Scheme is hereby established.

**፱. <u>ስለጡረታ ፈንዶች መቋቋም</u>**

የሚከተሉት የመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ ፈንዶች በዚህ አዋጅ ተቋቁመዋል፡-

፩/ የሲቪል መንግሥታዊ አገልግሎት ጡረታ ፈንድ፤

፪/ የወታደራዊ እና የፖሊስ አገልግሎት ጡረታ ፈንድ፡፡

**፲. <u>የሲቪል መንግሥታዊ አገልግሎት ጡረታ ፈንድ መዋጮ</u>**

ለሲቪል መንግሥታዊ አገልግሎት ጡረታ ፈንድ በመንግሥት ሠራተኛው ደመወዝ ላይ ተመስርቶ የሚደረገው መዋጮ እንደሚከተለው ይሆናል፡-

፩/ በመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ፲፩ በመቶ፤

፪/ በመንግሥት ሠራተኛው ፯ በመቶ፡፡

**፲፩. <u>የወታደራዊ እና የፖሊስ አገልግሎት ጡረታ ፈንድ መዋጮ</u>**

ለወታደራዊ እና ለፖሊስ አገልግሎት ጡረታ ፈንድ በመንግሥት ሠራተኛው ደመወዝ ላይ ተመስርቶ የሚደረገው መዋጮ እንደሚከተለው ይሆናል፡-

፩/ በመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ፴፫ በመቶ፤

፪/ በመንግሥት ሠራተኛው ፯ በመቶ፡፡

**፲፪. <u>የጡረታ መዋጮ ክፍያ</u>**

፩/ እያንዳንዱ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የሠራተኞቹን የጡረታ መዋጮ ከደመወዛቸው ቀንሶና የራሱን መዋጮ ጨምሮ ለጡረታ ፈንዱ በየወሩ የመክፈል ግዴታ አለበት፤

**9. <u>Establishment of Pension Funds</u>**

The following Public Servants Pension Funds are hereby established:

1/ the Civil Service Pension Fund;

2/ the Military and Police Service Pension Fund.

**10. <u>Contributions to the Civil Service Pension Fund</u>**

The contributions payable to the Civil Service Pension Fund shall be based on the following salary of the public servants':

1/ by the public office, 11%;

2/ by the public servant, 7 %.

**11. <u>Contributions to the Military and Police Service Pension Fund</u>**

The contributions payable to the Military and Police Service Pension Fund shall be based on the following salary of the public servants':

1/ by the public office, 33 %;

2/ by the public servant, 7 %.

**12. <u>Payment of Pension Contributions</u>**

1/ Every public office shall deduct contributions of public servants from their salaries and pay the amount, together with its own contributions, to the pension fund monthly;

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) የተገለጸው የጡረታ መዋጮ ለሠራተኞች የወር ደመወዝ ከተከፈለበት ወር መጨረሻ ቀን አንስቶ በ፴ ቀናት ውስጥ ለጡረታ ፈንዱ ገቢ መደረግ አለበት፣

፫/ ከሠራተኞቹ ደመወዝ ሊቀነስ የሚገባውን መዋጮ ሳይቀንስ የቀረ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ክፍያውን ራሱ ለመፈጸም ኃላፊ ይሆናል፣

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በመንግሥት በጀት የሚተዳደሩ የፌደራልና የክልል መንግሥት መሥሪያ ቤቶችና የመንግሥት ሠራተኞች የጡረታ መዋጮ እንደአግባቡ በገንዘብ ሚኒስቴር እና በክልሎች የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት /ፋይናንስ/ ቢሮ ተሰብስቦ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፪) በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ለጡረታ ፈንዱ ገቢ ማድረግ አለባቸው፣

፭/ በራሳቸው ገቢ የሚተዳደሩ /ባለበጀት ያልሆኑ/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና የመንግሥት ሠራተኞች ወርሃዊ የጡረታ መዋጮ በአስተዳደሩ ወይም አስተዳደሩ በሚወክላቸው አካላት አማካኝነት ተሰብስቦ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ለጡረታ ፈንዱ ገቢ ይደረጋል፣

፮/ አስተዳደሩ በዚህ አንቀጽ የሚሰበሰበውን የጡረታ መዋጮ በትክክልና በወቅቱ ለጡረታ ፈንዱ ገቢ ስለመደረጉ በገንዘብ ሚኒስቴር፣ የክልል ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት /ፋይናንስ/ ቢሮዎች እንዲሁም በየደረጃው ያሉ በውክልና የጡረታ መዋጮ በሚሰበስቡ አካላት እና

2/ The contributions referred to in Sub-Article (1) of this Article shall be paid to the pension fund within 30 days from the last day of the month in which payment of salary has been effected;

3/ Where a public office fails to deduct contributions of public servants from their salaries, it shall be liable for payment of the same;

4/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) of this Article, contributions of federal and regional public offices fully or partly run by government allocated budgets and their public servants shall be collected and paid to the pension fund within the period specified under Sub-Article (2) of this Article as the case may be, by the Ministry of Finance and the regional Finance and Economic Development (finance) bureaus;

5/ Contributions of public offices run by their own income (non-budgetary) shall be collected and paid to the pension fund within the period specified under Sub-Article (2) of this Article by the Administration or the bodies to be delegated by the Administration;

6/ The Administration shall have the power to supervise, inspect (audit) and verify the proper computations of contributions collected by Ministry of Finance, the regional Finance and Economic Development (finance) bureaus, bodies

አሰሪ መሥሪያ ቤቶች በመገኘት የመቆጣጠርና ምርመራ (ኦዲት) በማድረግ የማጣራት እንዲሁም በተገቢው ጊዜ ገቢ በማያደርጉት ላይ ሕጋዊ እርምጃ የመውሰድ ሥልጣን ይኖረዋል፤

፯/ የክልል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሚፈለግባቸውን የጡረታ መዋጮ በወቅቱ ገቢ አለማድረጋቸውንና የገንዘቡ መጠን በአስተዳደሩ ሲገለጽለት የገንዘብ ሚኒስቴር የፌዴራሉ መንግሥት ድጎማ ከሚያደርግላቸው በጀት ላይ የመዋጮ ገንዘቡን ቀንሶ ለጡረታ ፈንዱ ገቢ ያደርጋል፤

፰/ አስተዳደሩ ወይም ውክልና የተሰጠው አካል ተገቢውን የጡረታ መዋጮ ለጡረታ ፈንዱ ገቢ ሳያደርግ ከ፫ ወር በላይ የቆየ የመንግሥት መሥሪያ ቤት መንግሥት ከሚመድብለት በጀት ወይም በባንክ ካለው ሂሳብ ላይ ተቀንሶ ገቢ እንዲሆን የማስደረግ ሥልጣን ይኖረዋል፤

፱/ የዚህን አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ ፰ ተግባራዊ ለማድረግ ማንኛውም ባንክ ወይም የፋይናንስ ተቋም በአስተዳደሩ ወይም በአስተዳደሩ ውክልና በተሰጠው አካል ሲጠየቅ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) መሠረት የሚሰበሰበውን የጡረታ መዋጮ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ከመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ሂሳብ ላይ ቀንሶ ለአስተዳደሩ ወይም በአስተዳደሩ ውክልና ለተሰጠው አካል ገቢ የማድረግ ግዴታ አለበት፤

delegated to collect pension contributions and public offices, and take legal action against public office who fails to pay contributions to be collected in accordance with this Article;

7/ The Ministry of Finance shall, upon being notified by the Administration the default of regional government offices in the timely payment of contributions and the amounts thereof, deduct the arrear contributions from their budgetary subsidies allocated by the federal government and pay same to pension fund;

8/ Where a public office fails to pay contributions for a period of more than three months, the Administration or the delegated body shall have the power to cause the deduction of the arrear contributions from the budget allocated to it by the government or from its bank account;

9/ For the implementation of Sub-Article 8 of this Article, any bank or financial institution shall, when requested by the Administration or the delegated body, has the obligation to deduct, without any precondition, the amount of contributions to be collected pursuant to Sub-Article (1) of this Article from the account of the public office and pay to the Administration or the delegated body;

፲/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፱) መሠረት ማንኛውም ባንክ ወይም የፋይናንስ ተቋም ከመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ሂሳብ ላይ ቀንሶ በአስተዳደሩ ወይም ውክልና በተሰጠው አካል ገቢ እንዲያደርግ ትዕዛዝ በጽሁፍ ከደረሰው በኋላ ከመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ሂሳብ ላይ ገንዘብ ወጪ አድርጎ ቢገኝ ባንኩ ወይም የፋይናንስ ተቋሙ ወጪ እንዲደረግ በፈቀደው የገንዘብ መጠን ልክ ተጠያቂ እና ኃላፊ ይሆናል፤

፲፩/ በጡረታ ዐቅዱ ለተሸፈኑ ሠራተኞች ደመወዝ የሚከፍል የመንግሥት መሥሪያ ቤት የባንክ ሂሳቡ የሚገኝበትን የባንክ ቅርንጫፍ ፣ የፋይናንስ ተቋምና የሂሳብ ቁጥሩን ለአስተዳደሩ በጽሁፍ የማሳወቅ የባንኩ ፣ የፋይናንስ ተቋሙ አድራሻና የሂሳብ ቁጥሩ ሲለወጥም ለውጡ ከተከሰተበት ቀን አንስቶ በ፲፭ ቀናት ውስጥ ለአስተዳደሩ በጽሁፍ የመግለጽ ግዴታ አለበት፤

፲፪/ አስተዳደሩ ወይም ውክልና የተሰጠው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፱) መሰረት ሊሰበሰብ ያልተቻለውን ውዝፍ የጡረታ መዋጮ /አስተዳደሩ/ የሚያወጣውን መመሪያ በመከተል በቀጥታ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱን ንብረት በጨረታ በመሸጥ ገቢ የማስደረግ ሥልጣን ይኖረዋል፤

፲፫/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፱ ንዑስ አንቀጽ (፯) መሠረት የሚወሰነው የጡረታ አበል በጡረታ ፈንድ ላይ ለሚያስከትለው ተጽዕኖ የመንግሥት ሠራተኛው በሕጉ መሠረት ጡረታ ለመውጣት ለሚቀረው ጊዜ የመጨረሻ ደመወዙን መሰረት በማድረግ በየወሩ ሊከፈል የሚገባው የጡረታ መዋጮ ታስቦ በቅድሚያ በመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ገቢ መደረግ አለበት፤

10/ In accordance with Sub-Article (9) of this Article, any bank or financial institution will be accountable to the amount of money withdrawn by public office after receving written order from the fund or delegated body to deduct the contribution debt from the public office account;

11/ Any public office which pays salary to public servants covered by pension scheme shall have the obligation to notify in writing to the Administration the branch of the bank and account number in which it has deposited money, and any change of address of the bank or account number within 15 days of the occurrence of such change.

12/ The Administration or the delegated body shall have the power to sell, through tender, the property of a public office for the purpose of collecting arrear contributions that could not be collected pursuant to Sub-Article (9) of this Article following the Directive to be issued by the Administration;

13/ For the purpose of compensating effects of benefits granted pursuant to Sub-Article (7) of Article 19 of this Proclamation to pension fund, the public office shall pay in advance the monthly contributions calculated for the remaining period that the public servant has to go through before he attains the retirement age;

፲፬/ ከኃላፊነት ለተነሱ ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊዎችና የምክር ቤት አባላት የሚከፈለው የጡረታ አበል በጡረታ ፈንድ ላይ ለሚያስከትለው ተጽዕኖ የጡረታ መውጫ ዕድሜ ለመድረስ ለሚቀረው ጊዜ በየወሩ ሊከፈል የሚገባው የጡረታ መዋጮ ታስቦ በገንዘብ ሚኒስቴር ለጡረታ ፈንዱ በቅድሚያ ገቢ መደረግ አለበት፤

፲፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፪) መሰረት የሚፈለግበትን የጡረታ መዋጮ በ፴ ቀን ውስጥ ገቢ ያላደረገ የመንግሥት የልማት ድርጅት ወይም በራሱ ገቢ የሚተዳደር የመንግሥት መሥሪያ ቤት ገቢ ባልተደረገው የጡረታ መዋጮ ላይ ደመወዝ ከተከፈለበት ቀጥሎ ካለው ወር የመጀመሪያ ቀን አንስቶ በባንክ ማስቀመጫ ወለድ መጠን መሠረት ከሚታሰብ ወለድ እና አምስት በመቶ ቅጣት ጨምሮ የመክፈል ግዴታ ይኖርበታል፤

፲፮/ ከጡረታ መዋጮ ገንዘብ ላይ ቀንሶ ለአገልግሎት ክፍያ፣ ለገንዘብ ማስተላለፊያ፣ ለዕዳ መክፈያ ወይም ለማንኛውም አገልግሎት መጠቀም የተከለከለ ነው፤

፲፯/ አስተዳደሩ የጡረታ መዋጮ ገቢን ከመሰብሰብና ከማስፈጸም ጋር የተያያዙ ማናቸውንም ሥራዎች ለሌሎች አካላት ውክልና በመስጠት ማሠራት ይችላል፤

፲፰/ የጡረታ መዋጮ ክፍያ ከማንኛውም ዕዳ ክፍያ ቅድሚያ ይኖረዋል፡፡

14/ For the purpose of compensating effect of benefits granted to an outgoing senior government official or member of parliament to pension fund, the Ministry of Finance shall pay in advance the monthly contributions calculated for the remaining period that the official or member has to go through before he attaines the retirement age;

15/ If the public enterprise or self-financing public office fails to pay pension contribution collected pursuant to Sub Article (2) of this Article within 30 days, it shall be liable to pay interest with the bank deposit interest rate and in addition 5% penalty for the unpaid pension contribution calculated from the first day of the month following the last day of the month in which payment of salary has been effected;

16/ It is prohibited to deduct from pension contributions for payment of service charges, money transfer, charges or debt or for any other purpose;

17/ The Administration may delegate activities in relation to the collection and enforcement of pension contributions to other bodies;

18/ The payment of pension contributions shall have priority over any debt.

**፲፫. <u>የጡረታ ፈንዶች አስተዳደር</u>**

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፱ የተቋቋሙትን የጡረታ ፈንዶች የሚያስተዳድረው የመንግሥት ሠራተኞች ማኅበራዊ ዋስትና ፈንድ አስተዳደር ይሆናል፡፡

**፲፬. <u>የጡረታ ፈንዶች አጠቃቀም</u>**

፩/ የጡረታ ፈንዶቹ ጥቅም ላይ የሚውሉት፡-

ሀ) በዚህ አዋጅ የተመለከቱትን የጡረታ አበል ክፍያዎች ለመፈጸም፣

ለ) በአስተዳደሩ ሥራ አመራር ቦርድ በሚወሰኑ አትራፊና አስተማማኝ ኢንቨስትመንቶች ላይ ለማዋል፤ እና

ሐ) ለአስተዳደሩ አስተዳደራዊ ወጪዎች፣ ብቻ ይሆናል፡፡

፪/ የጡረታ ፈንዶች በማናቸውም የዕዳ ክፍያ ምክንያት ሊከበሩ ወይም ሊያዙ አይችሉም፡፡

**፲፭. <u>የአክቹዋሪ ግምገማ</u>**

፩/ "የአክቹዋሪ ግምገማ" ማለት የጡረታ ዐቅድ ስታስቲካዊ መረጃዎችን የኢንቨስትመንት አፈጻፀምን፣ የኢኮኖሚ እና ሥነ-ሕዝብ ግምታዊ መረጃዎችን በማጠናቀርና በመተንተን የጡረታ ፈንዱ ያለበት ደረጃ የሚለይበት፣ ስጋቶችና የወደፊት ሁኔታ ትንበያ የሚከናወንበት የግምገማ ዘዴ ነው፡፡

፪/ የመንግሥት ሠራተኞች የጡረታ ዐቅድ በየአምስት ዓመቱ በሂሳብ ስሌት ባለሙያዎች /አክቹዋሪስት/ እንዲገመገም ይደረጋል፡፡

**13. <u>Administration of Pension Funds</u>**

The pension funds established under Article 9 of this Proclamation shall be administered by the Public Sevants Social Security Administration.

**14. <u>Utilization of Pension Funds</u>**

1/ The pension funds shall be utilized only for:

a) Effecting payments of pension benefits stipulated under this Proclamation;

b) Profitable and reliable investments to be decided by the Administrations' Management Board; and

c) covering the operational expenses of the Administration.

2/ Pension funds may not be attached or secured in respect of any debt.

**15. <u>Actuarial Analysis and Evaluation</u>**

1/ "Actuarial Valuation " is a method of compiling and analyzing the pension scheme's statistical data, investment performance, economic and demographic estimates, and identifying the pension fund status, risk and future projections.

2/ The Public Servant Pension Scheme shall be evaluated by actuaries every Five years.

## ክፍል አራት

## ስለ አገልግሎት ዘመንና የጡረታ መውጫ ዕድሜ

### ፲፮. የአገልግሎት ዘመን መቆጠር ስለሚጀመርበት ጊዜ

፩/ የመንግስት ሠራተኛ የአገልግሎት ዘመን መቆጠር የሚጀምረው በመንግሥት ሠራተኛነት ከተቀጠረበት ወይም ከተመደበበት ቀን አንስቶ ነው፡፡

፪/ ወደ መንግሥት ይዞታ በተዛወረ ድርጅት ውስጥ የሚሠራ የመንግሥት ሠራተኛ በዚህ አዋጅ ድንጋጌ መሰረት የሚከፈለውን የጡረታ መዋጮ ሊሸፍን የሚችል ፕሮቪደንት ፈንድ ያለው ከሆነ ገንዘቡ ሙሉ በሙሉ ለጡረታ ፈንዱ ገቢ ሆኖ መዋጮ መክፈል ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ያለው አገልግሎት ይያዝለታል፣ ሆኖም የፕሮቪደንት ፈንድ የሌለው ከሆነ ድርጅቱ ወደ መንግሥት ከተዛወረበት ጊዜ አንስቶ አገልግሎቱ ይያዝለታል፡፡

፫/ የመንግሥት ሠራተኛው በግል ድርጅቶች ሠራተኞች የጡረታ ዐቅድ በሚሸፈን የግል ድርጅት የፈጸመው አገልግሎት በዐቅዱ መዋጮ መክፈል ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ይያዝለታል፡፡ ለዚህ አገልግሎት አያያዝ የግል ድርጅቶች ሠራተኞች ጡረታ ፈንድ የሚያስተዳድረው አካል የሠራተኛውን የግል መረጃና ማስረጃ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለአስተዳደሩ ማዛወር አለበት፡፡

## PART FOUR

## PERIOD OF SERVICE AND RETIREMENT AGE

### 16. Commencement of Period of Service

1/ The period of service of a public servant shall begin with the date of his employment or appointment.

2/ Where a public servant working in an enterprise transferred to government ownership has a provident fund which fully covers the contribution due in accordance with the provisions of this Proclamation, the fund shall be paid to the pension fund and his service since the start of the contribution shall be counted; provided, however, that if he has no provident fund, his service shall begin to count as of the date of such transfer.

3/ The service that a public servant has rendered in a private organization covered by the Private Organizations Employees' Pension Scheme shall be counted as of the date of starting payment of contribution in accordance with the Scheme. For the purpose of counting the service, the organ which administers the Private Organizations Employees' Pension Fund shall transfer, within one month, the personal records of the public servant to the Administration.

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፫) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በመንግሥት መሥሪያ ቤት ለተፈጸመ አገልግሎት አያያዝ ከመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ ፈንድ ወደ ግል ድርጅቶች ሠራተኞች ጡረታ ፈንድ እንዲሁም በግል ድርጅት ለተፈፀመ አገልግሎት ከግል ድርጅቶች ሠራተኞች ጡረታ ፈንድ ወደ መንግሥት ሠራተኞች ጡረታ ፈንድ የሚደረገውን የጡረታ መዋጮ ገንዘብ ትልልፍ በተመለከተ ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

## ፲፯. የአገልግሎት ዘመን አቆጣጠር

፩/ የአገልግሎት ዘመን የሚቆጠረው በሙሉ ዓመታት፣ በወራትና በቀናት ታስቦ ነው፤

፪/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፮ ንዑስ-አንቀጽ (፪) እና (፫) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ለማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ በተለያዩ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና የግል ድርጅቶች ሠራተኞች ጡረታ ዐቅድ ሽፋን ባለው ድርጅት የፈፀመው የአገልግሎት ዘመን በሙሉ ተዳምሮ ይታሰባል፤

፫/ ለማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ የሚከተለው አገልግሎቱ ይታሰብለታል፡-

ሀ) ከጡረታ መውጫ ዕድሜ በኋላ አገልግሎቱ በሕግ መሰረት ተራዝሞለት በሥራ ላይ እንዲቆይ የተደረገበት ጊዜ፤

ለ) የጡረታ መውጫ ዕድሜው በመድረሱ አበል ከተወሰነለት በኋላ በመንግሥት ውሳኔ ወደ ሥራ ተመልሶ አገልግሎት የሰጠበት ጊዜ፤

4/ Subject to the provisions of Sub-Article (3) of this Article, the issue of transfer of pension contributions from the Public Service Pension Fund to the Private Sector Employees' Pension Fund and the transfer of funds from the Private Sector Employees' Pension Fund to the Public Service Pension Fund shall be determind based on the Directive issued by the National bank.

## 17. Calculation of Period of Service

1/ Period of service shall be calculated in complete years, months and days;

2/ Without prejudice to Sub-Article (2) and (3) of Article 16 of this Proclamation, the period of service of a public servant shall include all services rendered to different public offices and private organizations covered by the Private Organizations Employees' Pension Scheme;

3/ For any public servant the following shall be counted as period of service:

a) period of service beyond retirement age, if lawfully retained in service;

b) period of service spent after reengagement upon a government decision subsequent to retirement due to age;

ሐ) የደመወዝ ክፍያ ሳይቋረጥ በማናቸውም ምክንያት አገልግሎቱ ተቋርጦ የቆየበት ጊዜ፣

መ) በየወሩ ደመወዝ እየተከፈለው ሙሉ ጊዜውን በማናቸውም የመንግሥት አካል ወይም በሠራተኛ ማህበር በተመራጭነት አገልግሎት የሰጠበት ጊዜ፣

ሠ) በመንግሥት መሥሪያ ቤት በጊዜያዊነት አገልግሎት የሰጠበት ጊዜ፣

ረ) በመንግሥት ትዕዛዝ መንግሥት ከ፶ በመቶ በታች የካፒታል ድርሻ በያዘበት ድርጅት በማገልገል ያሳለፈው ጊዜ፣

ሰ) በመንግሥት ውሳኔ በዓለም አቀፍ ድርጅት በማገልገል ያሳለፈው ጊዜ፣

ሸ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፬) ፊደል ተራ (ሀ) የተደነገገው ቢኖርም ከጡረታ መውጫ ዕድሜ በኋላ በምክር ቤት አባልነት አገልግሎት የሰጠበት ጊዜ፡፡

፬/ ለማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ በዚህ አንቀጽ መሰረት ለሚያዝለት የአገልግሎት ዘመን የሚከተለው አይታሰብለትም፡-

ሀ) አገልግሎቱ በሕጉ መሠረት ካልተራዘመ በስተቀር የጡረታ መውጫ ዕድሜው ከደረሰበት ከሚቀጥለው ወር አንስቶ የሚሰጠው አገልግሎት፣

ለ) ኢትዮጵያ ተዋዋይ ወገን የሆነችበት ማናቸውም ዓለም አቀፍ ስምምነትና የዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፫) ፊደል ተራ (ሠ) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በሕጋዊ ፈቃድ የኢትዮጵያ ዜጋ የሆነ የመንግስት ሠራተኛ

c) period of service which was interrupted due to any cause without interruption of payment of salary;

d) period of service spent in any public body or trade union as salaried fulltime elected member;

e) period of service rendered in a public office as a temporary worker;

f) period of service spent, upon a government order, in an enterprise where the government capital share is less 50 percent;

g) period of service spent, upon a government decision, in an international organization;

h) Notwithstanding Sub-Article (4) paragraph (a) of this Article, service rendered as member of parliament beyond retirement age.

4/ For any public servant the following shall not be counted as period of service:

a) unless lawfully retained in service, the service he renders as of the first day of the month following that in which he attains retirement age;

b) without prejudice to any International Treaty to which Ethiopia is a party and Sub-Article (3) paragraph (e) of this Article, the service rendered by a naturalized Ethiopian in any public

የኢትዮጵያን ዜግነት ከማግኘቱ በፊት በመንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም በጡረታ ዐቅድ በተሸፈነ የግል ድርጅት የሰጠው አገልግሎት፡፡

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፫) ከፊደል ተራ (ሐ) እስከ (ሸ) የተመለከተው ጊዜ በአገልግሎት ዘመንነት ሊታሰብ የሚችለው ሠራተኛው ወይም ተመራጩ መክፈል ያለበትን የጡረታ መዋጮ የአሠሪውን ድርሻ ጨምሮ ራሱ የከፈለ ወይም እንዲከፈልለት ያደረገ እንደሆነ ነው፤

፮/ በዚህ አዋጅ ወይም በግል ድርጅቶች ሠራተኞች የጡረታ አዋጅ መሰረት የአገልግሎት ወይም የጤና ጉድለት ዳረጎት ተከፍሎት የተሰናበተ የመንግሥት ሠራተኛ ወይም የግል ድርጅት ሠራተኛ እንደገና በመንግሥት ሠራተኛነት የተቀጠረ ወይም የተመደበ ከሆነና የወሰደውን ዳረጎት መልሶ ገቢ ካደረገ የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፮ ንዑስ-አንቀጽ (፫) እንደተጠበቀ ሆኖ የቀድሞው አገልግሎቱ ይታሰብለታል፤

፯/ በዚህ አዋጅ ወይም በግል ድርጅቶች ሠራተኞች የጡረታ አዋጅ መሰረት ከሐምሌ ፩ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም በፊት የጡረታ መዋጮ ተመላሽ ተደርጎለት የነበረ ሰው እንደገና በመንግሥት ሠራተኛነት የተቀጠረ ወይም የተመደበ ከሆነና የወሰደውን የጡረታ መዋጮ ተመላሽ ከባንክ የማስቀመጫ ወለድ ጭምር መልሶ ገቢ ካደረገ የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፯ ንዑስ-አንቀጽ (፫) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የቀድሞው አገልግሎቱ ይታሰብለታል፤

office or private organization covered by pension scheme before his naturalization.

5/ Period of service referred to under Sub-Article (3) from paragraph (c) to (h) of this Article shall be counted as period of service only where the public servant or elected member pays the contributions by himself including that of the employer or causes the employer to effect payments of same;

6/ Where a person who has received gratuity payment pursuant to this Proclamation or the Private Organization Employees' Pension Proclamation is re-employed or assigned as a public servant, his former service shall, without prejudice to Sub-Article (3) of Article 16 of this Proclamation, be counted along with the new service; provided, however, that the gratuity he received shall be paid back;

7/ A person to whom prior to July 08, 2015 reimbursement of pension contribution has been made pursuant to this Proclamation or the Private Organization Employees' Pension Proclamation, is re-employed or assigned as a public servant, his former service shall, without prejudice to Article 17 Sub-Article (3) of this Proclamation, be counted along with the new service; provided, however, that the reimbursed contribution shall be paid back with interest calculated at bank deposit interest rate;

የኢትዮጵያን ዜግነት ከማግኘቱ በፊት በመንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም በጡረታ ዐቅድ በተሸፈነ የግል ድርጅት የሰጠው አገልግሎት፡፡

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፫) ከፊደል ተራ (ሐ) እስከ (ሸ) የተመለከተው ጊዜ በአገልግሎት ዘመንነት ሊታሰብ የሚችለው ሠራተኛው ወይም ተመራጩ መክፈል ያለበትን የጡረታ መዋጮ የአሠሪውን ድርሻ ጨምሮ ራሱ የከፈለ ወይም እንዲከፈልለት ያደረገ እንደሆነ ነው፤

፮/ በዚህ አዋጅ ወይም በግል ድርጅቶች ሠራተኞች የጡረታ አዋጅ መሰረት የአገልግሎት ወይም የጤና ጉድለት ዳረጎት ተከፍሎት የተሰናበተ የመንግሥት ሠራተኛ ወይም የግል ድርጅት ሠራተኛ እንደገና በመንግሥት ሠራተኛነት የተቀጠረ ወይም የተመደበ ከሆነና የወሰደውን ዳረጎት መልሶ ገቢ ካደረገ የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፮ ንዑስ-አንቀጽ (፫) እንደተጠበቀ ሆኖ የቀድሞው አገልግሎቱ ይታሰብለታል፤

፯/ በዚህ አዋጅ ወይም በግል ድርጅቶች ሠራተኞች የጡረታ አዋጅ መሰረት ከሐምሌ ፩ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም በፊት የጡረታ መዋጮ ተመላሽ ተደርጎለት የነበረ ሰው እንደገና በመንግሥት ሠራተኛነት የተቀጠረ ወይም የተመደበ ከሆነና የወሰደውን የጡረታ መዋጮ ተመላሽ ከባንክ የማስቀመጫ ወለድ ጭምር መልሶ ገቢ ካደረገ የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፯ ንዑስ-አንቀጽ (፫) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የቀድሞው አገልግሎቱ ይታሰብለታል፤

office or private organization covered by pension scheme before his naturalization.

5/ Period of service referred to under Sub-Article (3) from paragraph (c) to (h) of this Article shall be counted as period of service only where the public servant or elected member pays the contributions by himself including that of the employer or causes the employer to effect payments of same;

6/ Where a person who has received gratuity payment pursuant to this Proclamation or the Private Organization Employees' Pension Proclamation is re-employed or assigned as a public servant, his former service shall, without prejudice to Sub-Article (3) of Article 16 of this Proclamation, be counted along with the new service; provided, however, that the gratuity he received shall be paid back;

7/ A person to whom prior to July 08, 2015 reimbursement of pension contribution has been made pursuant to this Proclamation or the Private Organization Employees' Pension Proclamation, is re-employed or assigned as a public servant, his former service shall, without prejudice to Article 17 Sub-Article (3) of this Proclamation, be counted along with the new service; provided, however, that the reimbursed contribution shall be paid back with interest calculated at bank deposit interest rate;

፰/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት አስተዳደሩ በሚያቀርብለት ጥናት መሰረት በከባድ ወይም ለጤንነትና ለሕይወት አስጊ በሆኑ የሥራ መስኮች የተፈጸመ አገልግሎት እስከ እጥፉ እንዲቆጠር ሊወስን ይችላል፡፡

**፲፰. <u>የጡረታ መውጫ ዕድሜ</u>**

፩/ የጡረታ መውጫ ዕድሜ የመንግሥት ሠራተኛው ለመጀመሪያ ጊዜ ሲቀጠር በቅድሚያ የመዘገበውን የልደት ዘመን መሠረት በማድረግ እንደሚከተለው ይሆናል፡-

ሀ) ለመከላከያ ሠራዊት አባላት በሠራዊቱ መተዳደሪያ ሕግ በሚወሰን ዕድሜ፣

ለ) ለፖሊስ አባላት በፖሊስ መተዳደሪያ ሕግ በሚወሰን ዕድሜ፣

ሐ) ለሌሎች የመንግሥት ሠራተኞች ፷ ዓመት፡፡

፪/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት አስተዳደሩ በሚያቀርብለት ጥናት መሠረት በልዩ ሁኔታ ለሚታዩ የሙያ መስኮች በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) ከተመለከተው በላይ የሆነ የጡረታ መውጫ ዕድሜ ሊወስን ይችላል፣

፫/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት አስተዳደሩ በሚያቀርብለት ጥናት መሠረት በከባድ ወይም ለጤንነትና ለሕይወት አስጊ በሆኑ የሥራ መስኮች ላይ ለተሰማሩ የመንግሥት ሠራተኞች በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) ከተመለከተው ያነሰ የጡረታ መውጫ ዕድሜ ሊወስን ይችላል፡፡

8/ On the basis of studies submitted to it by the Administration, the Council of Ministers may decide that period of service spent on hazardous jobs or on jobs involving risks to health and life be counted up to twice the actual period of service.

**18. <u>Retirement Age</u>**

1/ The retirement age of a public servant shall, based on the date of birth registered when he was employed for the first time, be:

a) for a member of the defense force, the age determined by the law regulating to the administration of the defense force;

b) for a member of the police, the age determined by the law regulating the administration of the police;

c) for other public servant, 60 years.

2/ On the basis of studies submitted to it by the Administration, the Council of Ministers may determine retirement age higher than the age provided under Sub-Article (1) of this Article with respect to professions that may deserve special consideration;

3/ On the basis of studies submitted to it by the Administration, the Council of Ministers may determine retirement age lesser than the age provided under Sub-Article (1) of this Article for public servants working on hazardous jobs or on jobs involving risks to health and life.

## ክፍል አምስት

## ስለአገልግሎት ጡረታ አበልና ዳረጎት

### ፲፱. የአገልግሎት ጡረታ አበል

፩/ ቢያንስ ፲ ዓመት ያገለገለ የመንግሥት ሠራተኛ የጡረታ መውጫ ዕድሜው በመድረሱ ከሥራ ሲሰናበት የአገልግሎት ጡረታ አበል እስከ ዕድሜ ልኩ ይከፈለዋል፣

፪/ ቢያንስ ፲ ዓመት ያገለገለ የመንግሥት ሠራተኛ ከሐምሌ ፩ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም ጀምሮ በራሱ ፈቃድ ወይም በዚህ አዋጅ ከተጠቀሱት ውጪ በሆነ ምክንያት አገልግሎት ካቋረጠ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፲፰ ንዑስ-አንቀጽ (፩) በተደነገገው መሠረት የጡረታ መውጫ ዕድሜው ሲደርስ የአገልግሎት ጡረታ አበል እስከ ዕድሜ ልኩ ይከፈለዋል፤

፫/ ቢያንስ ፳፭ ዓመት ያገለገለ የመንግሥት ሠራተኛ በራሱ ፈቃድ ወይም በዚህ አዋጅ ከተጠቀሱት ውጭ በሆነ ምክንያት አገልግሎት ካቋረጠ የጡረታ መውጫ ዕድሜው ሊደርስ አምስት ዓመት ከሚቀረው ጊዜ ጀምሮ እስከ ዕድሜ ልኩ የአገልግሎት ጡረታ አበል ይከፈለዋል፤

፬/ ዕድሜው ለጡረታ ሲደርስ የጡረታ መብት መከበሩ እንደተጠበቀ ሆኖ የዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፫) ድንጋጌ በዲስፕሊን ጉድለት ምክንያት አገልግሎቱ ለተቋረጠ የመንግሥት ሠራተኛ ተፈፃሚ አይሆንም፤

## PART FIVE

## RETIREMENT PENSION AND GRATUITY

### 19. Retirement Pension

1/ A public servant who has completed at least 10 years of service and retires upon attaining retirement age shall receive retirement pension for life;

2/ A public servant who has completed at least 10 years and separates from the service by voluntary resignation or for any other cause other than those provided for in this Proclamation, commencing from the date of July 08, 2015, shall receive retirement pension for life upon attaining retirement age pursuant to Sub-Article (1) of Article 18 of this Proclamation;

3/ A public servant who has completed at least 25 years and separates from the service by voluntary resignation or for any other cause other than those provided for in this Proclamation, shall receive retirement pension for life beginning with five years prior to retirement age;

4/ Without prejudice to the entitlement of pension right upon attainment of retirement age, the provisions of Sub-Article (3) of this Article shall not be applicable to a public servant who separates from the service on grounds of disciplinary measures;

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም ቢያንስ አንድ ሙሉ የምርጫ ዘመን ያገለገለ ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊ ወይም የምክር ቤት አባል ከኃላፊነት ሲነሳ ዕድሜው ፶ ዓመት የሞላው ከሆነ የአገልግሎት ጡረታ አበል እስከ ዕድሜ ልኩ ይከፈለዋል፤

፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፪) ወይም (፫) ወይም (፬) መሠረት አገልግሎቱ የተቋረጠ የመንግሥት ሠራተኛ የጡረታ መውጫ ዕድሜው ሳይደርስ በጤና ጉድለት ምክንያት ለሥራ ብቁ አለመሆኑ ከተረጋገጠ ይኸው ከተረጋገጠበት ጊዜ ቀጥሎ ካለው ወር ጀምሮ የአገልግሎት ጡረታ አበል እስከ ዕድሜ ልኩ ይከፈለዋል፡፡ የሞተ እንደሆነም ከሞተበት ጊዜ ቀጥሎ ካለው ወር ጀምሮ ለተተኪዎች አበል ይከፈላል፤

፯/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ህልውና በማክተሙ የሰው ኃይል ብዛት ከሚፈልገው በላይ በመሆኑ ወይም ከፕራይቬታይዜሽን ጋር በተያያዘ ከሥራ እንዲሰናበት ከተደረገና አገልግሎቱ ከ፳፭ ዓመት ያላነሰና ዕድሜው ከ፶ ዓመት ያላነሰ ከሆነ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ሲወሰን የአገልግሎት ጡረታ አበል እስከ ዕድሜ ልክ ይከፈለዋል፡፡

## ፳. የአገልግሎት ጡረታ አበል መጠን

፩/ ለማንኛውም ፲ ዓመት ላገለገለ የመንግሥት ሠራተኛ የሚከፈለው የአገልግሎት ጡረታ አበል መጨረሻ ባገለገለባቸው ሦስት ዓመታት ውስጥ ይከፈለው የነበረው አማካይ ደመወዝ

5/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) of this Article, a senior government official or a member of parliament, who has served at least one full term and has attained the age of 50 years when he leaves office shall receive retirement pension for life;

6/ Where it is ascertained that a public servant who has separated from service in accordance with Sub-Article (2) or (3) or (4) of this Article becomes incapable of fulfilling the medical conditions of service due to health problems prior to attaining the retirement age, he shall receive retirement pension for life starting with the month following such ascertainment; in case he dies, his survivors shall be paid benefits starting with the month following his death;

7/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) of this Article, a public servant who separates from the service due to the fact that the public office has ceased to exist, due to reduction of work force or for reasons relating to privatization, and his service and age are not less than 25 years and 50 years, respectively, shall, upon the decision of the Council of Ministers, receive retirement pension for life.

## 20. Amount of Retirement Pension

1/ The retirement pension of any public servant who has completed 10 years of service shall be 30% of his average salary for the last three years preceding

፴ በመቶ ሆኖ ከ፲ ዓመት በላይ ለፈጸመው ለእያንዳንዱ ዓመት አገልግሎት፡-

ሀ) የመከላከያ ሠራዊት ወይም የፖሊስ አባል ላልሆነ የመንግሥት ሠራተኛ ፩ነጥብ፳፭ በመቶ፤

ለ) ለመከላከያ ሠራዊት ወይም ለፖሊስ አባል ፩ነጥብ፷፭ በመቶ ተጨምሮ ይታሰባል፡፡

፪/ ቢያንስ አንድ ሙሉ የምርጫ ዘመን ላገለገለ ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊ ወይም የምክር ቤት አባል መጨረሻ ባገለገለባቸው ሦስት ዓመታት ውስጥ ይከፈለው የነበረው አማካይ ደመወዝ ፲፭ በመቶ፣ ከአምስት ዓመት በላይ ለተፈጸመ ለእያንዳንዱ አገልግሎት ዘመን ፩ነጥብ፩፻፳፭ በመቶ ተጨምሮ ይታሰባል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) ወይም (፪) መሠረት የሚወሰነው የአበል መጠን የመንግሥት ሠራተኛው፣ ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊው ወይም የምክር ቤት አባሉ መጨረሻ ባገለገለባቸው ሦስት ዓመታት ውስጥ ይከፈለው ከነበረው አማካይ ደመወዝ ፸ በመቶ ሊበልጥ አይችልም፡፡

፬/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ-አንቀፅ (፫) የተጠቀሰው ጠቅላላ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ አስተዳደሩ ወቅታዊ የኑሮ ሁኔታን መሰረት አድርጎ ዝቅተኛ ወርሀዊ የጡረታ አበል መጠንና የጡረታ አበል ማስተካከያ ሲያደርግ ከተጠቀሰው መጠን ሊያልፍ ይችላል፡፡

retirement and shall be increased, for each year of service beyond 10 years:

a) by 1.25% for a public servant other than member of the defense force or the police;

b) by 1.65% for a member of the defense force or the police.

2/ The retirement pension of a senior government official or a member of parliament who has served at least one full term shall amount to 15% of his average salary for the last Three years preceding retirement and shall be increased by 1.125% for each year of service beyond five years.

3/ The retirement pension to be paid pursuant to Sub-Article (1) or (2) of this Article may not exceed 70% of the average salary of the public servant, senior government official or member of parliament for the last three years of service preceding retirement.

4/ Notwithstanding the general statement referred to in Sub-Article (3) of this Article, the minimum monthly pension and adjustment allowance may be exceeded when adjusted by the Administration on the basis of current living conditions.

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) እና (፪) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በግል ድርጅቶች ጡረታ አዋጅ በጡረታ ከሚገለልበት ሦስት ዓመት አስቀድሞ ባለው ወር ሲያገኝ ከነበረው መደበኛ የወር ደመወዝ በ፳፭ ከመቶ የሚበልጥ ዓመታዊ አማካይ ክፍያ ስለሚከፈለው የግል ድርጅት ሠራተኛ የአማካይ የደመወዝ አያያዝ የተደነገገው በተመሳሳይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**፳፩. <u>የአገልግሎት ዳረጎት</u>**

፩/ ከአሥር ዓመት ያነሰ አገልግሎት የፈጸመ የመንግሥት ሠራተኛ የጡረታ መውጫ ዕድሜው በመድረሱ ከሥራ ሲሰናበት የአገልግሎት ዳረጎት ይከፈለዋል፣

፪/ ከአንድ ሙሉ የምርጫ ዘመን ያነሰ አገልግሎት ያለው ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊ ወይም የምክር ቤት አባል ከኃላፊነት ሲነሣ ዕድሜው ፶ ዓመት ወይም በላይ ከሆነ የአገልግሎት ዳረጎት ይከፈለዋል፡፡

**፳፪/ <u>የአገልግሎት ዳረጎት መጠን</u>**

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፩ መሠረት የሚከፈለው ዳረጎት፡-

፩/ የመከላከያ ሠራዊት ወይም የፖሊስ አባል ላልሆነ የመንግሥት ሠራተኛ ከሥራ ከተሰናበተበት ወር በፊት ይከፈለው የነበረው የ፩ነጥብ፳፭ በመቶ የወር ደመወዝ በአገለገለበት ዓመት ቁጥር ተባዝቶ ይታሰባል፣

፪/ ለመከላከያ ሠራዊት ወይም ለፖሊስ አባል ከሥራ ከተሰናበተበት ወር በፊት ይከፈለው የነበረው የ፩ነጥብ፷፭ በመቶ የወር ደመወዙ በአገለገለበት ዓመት ቁጥር ተባዝቶ ይታሰባል፣

5/ Notwithstanding the provisions of Sub-Articles (1) and (2) of this Article, the releavant provision of Private Organization Emplyees' Pension Proclamation regarding considering private organizations' employee who is paid a monthly salary which is above 25% annual average salary prior to three years of the employee's retirement shall be similarly applicable.

**21. <u>Retirement Gratuity</u>**

1/ A public servant who has not completed 10 years of service and retires on attaining retirement age shall receive gratuity;

2/ An outgoing senior government official or member of parliament who has served for less than one full term separates from service on attaining 50 or above years of age shall receive gratuity.

**22. <u>Amount of Retirement Gratuity</u>**

The gratuity payable in accordance with Article 21 of this Proclamation shall be:

1/ for a public servant other than member of the defense force or the police, his salary for 1.25 month preceding retirement multiplied by the number of years of service;

2/ for a member of the defense force or the police, his salary for 1.65 month preceding retirement multiplied by the number of years of service;

፫/ ለከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊ ወይም የምክር ቤት አባል ከኃላፊነት ከተነሳበት ወር በፊት ይከፈለው የነበረው የ፩ነጥብ፩፻፳፭ በመቶ የወር ደመወዝ በአገለገለበት ዓመት ቁጥር ተባዝቶ ይታሰባል፡፡

## ክፍል ስድስት

## ስለጤና ጉድለት ጡረታ አበልና ዳረጎት

### ፳፫. የጤና ጉድለት ጡረታ አበል

፩/ ቢያንስ ፲ ዓመት ያገለገለ የመንግሥት ሠራተኛ በጤና ጉድለት ምክንያት ደመወዝ የሚያስገኝ ማናቸውንም ሥራ መሥራት የማይችል በመሆኑ ከሥራ ሲሰናበት የጤና ጉድለት ጡረታ አበል እስከ ዕድሜ ልኩ ይከፈለዋል፣

፪/ ቢያንስ አንድ ሙሉ የምርጫ ዘመን ያገለገለ ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊ ወይም የምክር ቤት አባል በጤና ጉድለት ምክንያት ከኃላፊነት ከተነሣ የጤና ጉድለት የጡረታ አበል እስከ ዕድሜ ልኩ ይከፈለዋል፡፡

### ፳፬. የጤና ጉድለት ጡረታ አበል መጠን

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፫ መሠረት የሚከፈለው የጤና ጉድለት ጡረታ አበል በአንቀጽ ፳ መሠረት ይታሰባል፡፡

### ፳፭. የጤና ጉድለት ዳረጎት

፩/ ከ፲ ዓመት ያነሰ አገልግሎት የፈጸመ የመንግሥት ሠራተኛ በጤና ጉድለት ምክንያት ለሥራ ብቁ ባለመሆኑ ከሥራ ሲሰናበት የጤና ጉድለት ዳረጎት ይከፈለዋል፣

3/ for a senior government official or a member of parliament, his salary for 1.125 month preceding separation from service multiplied by the number of years of service.

## PART SIX

## INVALIDITY PENSION AND GRATUITY

### 23. Invalidity Pension

1/ A public servant who has completed at least 10 years of service and separates from service due to health problems preventing him from engaging in any remunerated work shall receive invalidity pension for life;

2/ A senior government official or member of parliament who has served at least one term and separates from service due to health problems shall receive invalidity pension for life.

### 24. Amount of Invalidity Pension

The invalidity pension payable in accordance with Article 23 of this Proclamation shall be calculated as provided under Article 20 hereof.

### 25. Invalidity Gratuity

1/ A public servant who has not completed 10 years of service and separates from service on becoming unfit for service due to health problems shall receive invalidity gratuity;

፪/ ከአንድ ሙሉ የምርጫ ዘመን ያነሰ አገልግሎት ያለው ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊ ወይም የምክር ቤት አባል በጤና ጉድለት ምክንያት ከኃላፊነት ከተነሣ የጤና ጉድለት ዳረጎት ይከፈለዋል፡፡

**፳፮. <u>የጤና ጉድለት ዳረጎት መጠን</u>**

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፭ መሰረት የሚከፈለው ዳረጎት በአንቀጽ ፳፪ መሠረት ይታሰባል፡፡

**፳፯. <u>የጡረታ መዋጮ ተመላሽ ስላለመደረጉ</u>**

የመንግሥት ሠራተኛው አገልግሎት በማናቸውም ምክንያት ቢቋረጥ የጡረታ መዋጮ ተመላሽ አይደረግም፡፡

**<u>ክፍል ሰባት</u>**

**<u>ስለጉዳት ጡረታ አበልና ዳረጎት</u>**

**፳፰. <u>ትርጓሜ</u>**

፩/ "በሥራ ላይ የሚደርስ ጉዳት" ማለት በሥራ ላይ የሚደርስ አደጋ ወይም በሥራ ምክንያት የሚመጣ በሽታ ነው፤

፪/ "በሥራ ላይ የሚደርስ አደጋ" ማለት የመንግሥት ሠራተኛው መደበኛ ሥራውን በማከናወን ላይ እንዳለ ወይም ከሥራ ጋር በተያያዘ ምክንያት በአካሉ ወይም በአካሉ የተፈጥሮ ተግባር ላይ በድንገት የሚደርስ ጉዳት ሲሆን የሚከተሉትን ይጨምራል፦

ሀ) የመንግሥት ሠራተኛው ከመደበኛ ሥራው ወይም መደበኛ የሥራ ቦታው ወይም ሰዓት ውጪ ስልጣኑ በሚፈቅድለት የሥራ ኃላፊ የተሰጠውን ትዕዛዝ በመፈጸም ላይ እያለ የደረሰን ጉዳት፤

2/ A senior government official or member of parliament who has served for less than one full term and separates from service due to health problems shall receive invalidity gratuity.

**26. <u>Amount of Invalidity Gratuity</u>**

The gratuity payable in accordance with Article 25 of this Proclamation shall be calculated as provided under Article 22 hereof.

**27. <u>Non-Reimbursement of Pension Contributions</u>**

If the service of a public servant is terminated due to any reason; the pension contribution may not be reimbursed.

**<u>PART SEVEN</u>**

**<u>EMPLOYMENT INJURY PENSION AND GRATUITY</u>**

**28. <u>Definitions</u>**

1/ "Employment injury" means occupational accident or occupational disease;

2/ "Occupational accident" means any organic injury or functional disorder suddenly sustained by a public servant during or in connection with the performance of his work and includes:

a) any injury sustained by a public servant while carrying out orders given by a competent authority outside of his regular work or working place or working hours;

ለ) ሥልጣኑ በሚፈቅድለት የሥራ ኃላፊ የተሰጠ ትዕዛዝ ባይኖርም የመንግሥት ሠራተኛው በመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ውስጥ የደረሰን ድንገተኛ አደጋ ወይም ጥፋት ለመከላከል በሥራ ሰዓት ወይም ከሥራ ሰዓት ውጪ በሚፈጽመው ተግባር ምክንያት የደረሰን ጉዳት፤

ሐ) የመንግሥት ሠራተኛው ወደ ሥራ ቦታው ወይም ከሥራ ቦታው የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ለመንግሥት ሠራተኞች አገልግሎት እንዲሰጥ በመደበው የመጓጓዣ አገልግሎት ወይም የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ለዚህ ተግባር በተከራየውና በግልጽ በመደበው የመጓጓዣ አገልግሎት በመጓዝ ላይ በነበረት ጊዜ የደረሰን ጉዳት፤

መ) የመንግሥት ሠራተኛው ከሥራው ጋር በተያያዘ ግዴታ የተነሳ ከሥራው በፊት ወይም በኋላ ወይም ሥራው ለጊዜው ተቋርጦ በነበረበት ጊዜ በሥራው ቦታ ወይም መሥሪያ ቤቱ ግቢ ውስጥ በመገኘት የደረሰበትን ማንኛውንም ጉዳት፤

ሠ) የመንግሥት ሠራተኛው ሥራውን በማከናወን ላይ ባለበት ጊዜ በመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ወይም በሦስተኛ ወገን ድርጊት ምክንያት የደረሰበትን ጉዳት፡፡

፫/ "በሥራ ምክንያት የሚመጣ በሽታ" ማለት የመንግሥት ሠራተኛው ከሚሠራው የሥራ ዓይነት ወይም ሥራውን ከሚያከናውንበት አካባቢ የተነሳ በሽታውን ለሚያስከትሉ ሁኔታዎች ተጋልጦ በመቆየቱ ምክንያት የደረሰ የጤና መታወክ ሲሆን ሥራውን በሚያከናውንበት ቦታ የሚዛመቱና የሚይዙ ነዋሪ ወይም ተላላፊ በሽታዎችን አይጨምርም፤

b) any injury sustained by a public servant during or outside of working hours while attempting to protect the public office from accident or destruction irrespective of an order given by a competent authority;

c) any injury sustained by a public servant while he is proceeding to or from his place of work in a transport service vehicle provided by the public office which is available for the common use of its employees or in a vehicle hired and expressly destined by the public office for the same purpose;

d) any injury sustained by a public servant before or after his work or during any interruption of work, if he is present in the work place or the premises of the public office by reason of his duties in connection with his work;

e) any injury sustained by a public servant as a result of an action of the public office or a third person during the performance of his work.

3/ "Occupational disease" means any pathological condition of a public servant which arises as a consequence of being exposed to the agent that cause the disease for a certain period prior to the date in which the disease became evident due to the kind of work he performs or because of the

surrounding in which he works; provided, however, that it does not include endemic or epidemic diseases which are prevalent and contracted in the area where the work is done;

፬/ "መደበኛ ሥራ" ማለት የመንግሥት ሠራተኛው በተሰጠው ኃላፊነት ወይም የሥራ ውል መሠረት የሚያከናውነው ተግባር ነው፤

፭/ "መደበኛ የሥራ ቦታ" ማለት የመንግሥት ሠራተኛው የመሥሪያ ቤቱን ሥራ ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ የሚያከናውንበት ሥፍራ ነው፡፡

4/ "Regular work" means the work performed by a public servant pursuant to his assignments or contract of employment;

5/ "Regular place of work" means a place where a public servant performs his duties for a definite or an indefinite duration.

**፳፱. <u>በራስ ላይ ጉዳት ስለማድረስ</u>**

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፰ የተመለከተው ተቀባይነት የሚኖረው የመንግሥት ሠራተኛው ጉዳቱ እንዲደርስበት ሆን ብሎ ያላደረገው ሲሆን ነው፡፡ በተለይም ቀጥሎ በተዘረዘሩት ምክንያቶች የደረሰ ጉዳት የመንግሥት ሠራተኛው በራሱ ላይ ሆን ብሎ ያደረሰው ጉዳት ሆኖ ይቆጠራል፡-

፩/ በመንግሥት መሥሪያ ቤቱ አስቀድሞ በግልጽ የተሰጡትን የደህንነት መጠበቂያ መመሪያዎች መጣስ ወይም የአደጋ መከላከያ ደንቦችን መተላለፍ፤ ወይም

፪/ አካሉ ወይም አዕምሮውን በሚገባ ለመቆጣጠር በማይችልበት ሁኔታ በመጠጥ ወይም በአደንዛዥ ዕጽ ሰክሮ በሥራ ላይ በመገኘት የደረሰ ጉዳት፡፡

**29. <u>Self Inflicted Injury</u>**

The provisions of Article 28 of this Proclamation shall apply only where the public servant has not inflicted the injury upon himself intentionally. Any injury resulting from, in particular, the following acts shall be deemed to be intentionally caused by the public servant:

1/ non-observance of safety instructions or preventive rules specifically issued by the public office; or

2/ reporting to work in a state of intoxication that prevents him from properly regulating his conduct or understanding.

**፴. በሥራ ምክንያት የሚመጣ በሽታና የአካል ጉዳት መጠን ሠንጠረዥ**

፩/ አስተዳደሩ አግባብ ካለው አካል ጋር በመመካከር ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም፡-

ሀ) የአካል ጉዳት መጠን፣

ለ) እያንዳንዱን በሥራ ምክንያት የሚመጣ በሽታን በሚመለከት፡-

(፩) የበሽታውን ምልክቶች፣

(፪) ለበሽታው መነሻ ይሆናል ተብሎ የሚታመነውን የሥራ ዓይነት ወይም አካባቢ፣

(፫) በሽታውን ለሚያሲዘው የሥራ ሁኔታ ለመጋለጥ የሚያስፈልገውን አነስተኛ ጊዜ የያዘ ዝርዝር ሠንጠረዥ በመመሪያ ያወጣል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) መሠረት የወጣው ሠንጠረዥ እንደአስፈላጊነቱ በየጊዜው ይሻሻላል፡፡

**፴፩. ግምት**

፩/ ከሥራው ቦታ ወይም ከሥራው ዓይነት ጋር የተያያዘ በሠንጠረዡ ውስጥ የተመለከተ በሽታ በተጠቀሰው የሥራ ቦታ ወይም የሥራ ዓይነት ላይ የተሰማራን የመንግሥት ሠራተኛ የያዘው እንደሆነ በሽታው በሥራ ምክንያት እንደመጣ ይቆጠራል፡፡

፪/ በሥራ ምክንያት በሚመጣ በሽታ ተይዞ የዳነ የመንግሥት ሠራተኛ በሠንጠረዡ ውስጥ በበሽታው አንጻር በተመለከተው

**30. Schedule of Occupational Disease and Degrees of Incapacity**

1/ For the implementation of this Proclamation the Administration shall, in consultation with the appropriate organ and by Directive, issue a schedule that lists:

a) the degrees of incapacity;

b) with respect to each occupational disease:

(1) the symptoms;

(2) the kind of work or surrounding that gives rise to the disease;

(3) the minimum duration of exposure to the agent causing the disease.

2/ The schedule issued in accordance with Sub-Article (1) of this Article shall be revised periodically as necessary.

**31. Presumption**

1/ Where a disease listed in the schedule is contracted by a public servant engaged in the corresponding work place or kind of work, it shall be presumed an occupational disease.

2/ Where a public servant who had recovered from an occupational disease is re-infected due to continued placement in

የሥራ ዓይነት ላይ ተመድቦ መስራት በመቀጠሉ በዚያው በሽታ እንደገና ቢያዝ አዲስ በሽታ እንደያዘው ይቆጠራል፡፡

፫/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፰ ንዑስ-አንቀጽ (፫) የተመለከተው ቢኖርም በመደበኛ ሥራው ምክንያት ተላላፊ ወይም ነዋሪ በሽታዎችን በማጥፋት ላይ የተሰማራ የመንግሥት ሠራተኛ በዚሁ በሽታ ከተያዘ በሥራ ምክንያት የመጣ በሽታ እንደያዘው ይቆጠራል፡፡

## ፴፪. ማስረጃ ማቅረብ ስለመቻሉ

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴ መሠረት በሚወጣው ሠንጠረዥ ውስጥ ያልተመለከተ በሽታ በሥራ ምክንያት የመጣ መሆኑን እንዲሁም በሠንጠረዡ ውስጥ የተመለከተ በሽታ በአንጻሩ ከተመለከቱት ምልክቶች በተለየ ሁኔታ የተከሰተ መሆኑን ለማረጋገጥ ማስረጃ ማቅረብ ይቻላል፡፡

## ፴፫. አደጋን ስለማስታወቅ

ከመከላከያ ሠራዊት አባል በስተቀር አንድ የመንግሥት ሠራተኛ በሥራ ላይ የሚደርስ ጉዳት የደረሰበት እንደሆነ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ አደጋው ከደረሰበት ቀን አንስቶ ባሉት ፴ ቀናት ውስጥ በጽሑፍ ለአስተዳደሩ ማስታወቅ አለበት፡፡ ይህ ባለመደረጉ በመንግሥት ሠራተኛው ላይ ለሚደርሰው ጉዳት መሥሪያ ቤቱ ኃላፊ ይሆናል፡፡

## ፴፬. ስለአካል ጉዳት መጠን አወሳሰን

፩/ በሥራ ምክንያት የሚመጣ ጉዳት መጠን የሚወሰነው ሥልጣን በተሰጠው የሕክምና ቦርድ ነው፤

the occupation corresponding to the disease listed in the schedule, he shall be presumed to have contracted the occupational disease afresh.

3/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (3) of Article 28 of this Proclamation, where a public servant engaged in the eradication of endemic or epidemic disease contracts same, it shall be presumed an occupational disease.

## 32. Admissibility of Evidence

Production of evidence may be permitted to proof that a disease not listed in the schedule to be issued under Article 30 of this Proclamation is of occupational origin, and that a disease listed in the schedule has been manifested in different symptoms from those indicated therein.

## 33. Notification of Accident

Where a public servant other than member of the defense force sustains occupational injury, the public office shall notify, in writing, the occurrence of same to the Administration within 30 days of such occurrence. Failure to do so shall make the public office liable for the damage sustained by the public servant.

## 34. Assessment of Employment Injury

1/ The extent of employment injury sustained by a public servant shall be assessed by authorized medical board;

፪/ ማንኛውም የሕክምና ቦርድ በሥራ ላይ የሚደርስ ጉዳት መጠንን የሚተምነው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴ በሚወጣ ሠንጠረዥ መሠረት ይሆናል፣

፫/ አስተዳደሩ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው በአንድ የሕክምና ቦርድ የተሰጠ ውሳኔ በሌላ በሕክምና ቦርድ እንደገና እንዲታይ ሊያደርግ ይችላል፣

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፫) መሠረት የቀረበ የሕክምና ቦርድ ውሳኔ እና በፊት በቀረበው መካከል ልዩነት ከተፈጠረ የሚወሰደው መረጃ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፬ መሠረት ይሆናል፡፡

**፴፭. የጉዳት አበል**

በሥራ ላይ በሚደርስ ጉዳት ምክንያት ከ፲ በመቶ ያላነሰ ሊድን የማይችል ጉዳት ለደረሰበት የመንግሥት ሠራተኛ እንደሁኔታው የጉዳት ጡረታ አበል ወይም የጉዳት ዳረጎት ይከፈለዋል፡፡

**፴፮. የጉዳት ጡረታ አበል**

አንድ የመንግሥት ሠራተኛ በሥራ ላይ በሚደርስ ጉዳት ምክንያት ከ፲ በመቶ ያላነሰ ሊድን የማይችል ጉዳት ደርሶበት ደመወዝ የሚያስገኝ ማናቸውንም ሥራ መሥራት የማይችል በመሆኑ ከሥራ ሲሰናበት የጉዳት ጡረታ አበል እስከ ዕድሜ ልኩ ይከፈለዋል፡፡

**፴፯. የጉዳት ጡረታ አበል መጠን**

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፮ መሠረት የሚከፈለው የጉዳት ጡረታ አበል መጠን የመንግሥት ሠራተኛው ጉዳቱ ከደረሰበት ወር በፊት ያገኝ የነበረው የወር ደመወዝ ፵፯ በመቶ ይሆናል፡፡

2/ Any medical board shall assess the extent of employment injury based on the schedule to be issued pursuant to Article 30 of this Proclamation;

3/ When it deems necessary, the Administration may refer the assessment to another medical board for further evaluation;

4/ If a decision made by one medical board in accordance with Sub-Article (3) of this Article is reconsidered by another medical board, the result shall be determined according to Article 54 of this Proclamation.

**35. Incapacity Benefit**

Incapacity pension for life or incapacity gratuity shall be paid, as the case may be, to a public servant who sustains employment injury of not less than 10 %.

**36. Incapacity Pension**

A public servant who sustains employment injury of not less than 10 % and separates from work due to permanent incapacity that prevents him from engaging in any remunerated work shall receive incapacity pension for life.

**37. Amount of Incapacity Pension**

1/ The amount of incapacity pension to be paid in accordance with Article 36 of this Proclamation shall be 47% of his salary which he was receiving during the month prior to the occurrence of the injury.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) መሠረት አበል ሊከፈለው የሚችል የመንግሥት ሠራተኛ በአገልግሎቱ ሊያገኝ የሚችለው አበል በጉዳት ሊያገኝ ከሚችለው የበለጠ ከሆነ የአገልግሎት ጡረታ አበል ይከፈለዋል፡፡

2/ If the retirement pension the public servant is entitled to is higher than the incapacity pension to be paid pursuant to Sub-Article (1) of this Article, he shall receive the retirement pension.

## ፴፰. የጉዳት ዳረጎት

፩/ አንድ የመንግሥት ሠራተኛ ከ፲ በመቶ ያላነሰ ከሥራ የመጣ ጉዳት ደርሶበት ሥራ ለመስራት የሚችል ከሆነ የጉዳት ዳረጎት ለአንድ ጊዜ ይከፈለዋል፤

፪/ የመንግሥት ሠራተኛው አግባብ ባለው ሕግ ወይም ኅብረት ስምምነት መሠረት በአሰሪው የጉዳት ካሣ ወይም የመድን ክፍያ የሚከፈለው ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) የተጠቀሰ የጉዳት ዳረጎት አይከፈለውም፡፡

## 38. Incapacity Gratuity

1/ A public servant who sustains employment injury of not less than 10 percent without loss of capacity to work shall receive incapacity gratuity in the form of a lump sum;

2/ If, in accordance with the appropriate law or collective agreement, the public servant is entitled to compensation for damage from the employer or insurance benefit, he shall not receive the incapacity gratuity to be paid pursuant to Sub-Article (1) of this Article.

## ፴፱. የጉዳት ዳረጎት መጠን

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፰ መሠረት የሚከፈለው የጉዳት ዳረጎት መጠን የመንግሥት ሠራተኛው ጉዳት ከደረሰበት ወር በፊት ይከፈለው የነበረው የወር ደመወዙ በ፵፯ በመቶ በ፷ ተባዝቶ የተገኘው ሂሳብ በመንግሥት ሠራተኛው ላይ በደረሰው ጉዳት መቶኛ ተባዝቶ ነው፡፡

## 39. Amount of Incapacity Gratuity

The amount of incapacity gratuity payable in accordance with Sub-Article (1) of Article 38 of this Proclamation shall be equal to 47% of the monthly salary of the public servant which he was receiving during the month preceding the occurrence of the injury multiplied by 60 and the percentage of injury sustained.

# ክፍል ስምንት

# የተተኪዎች ጡረታ አበልና ዳረጎት

## ፵. ጠቅላላ

፩/ ማንኛውም የመንግስት ሠራተኛ፡-

ሀ) የአገልግሎት ወይም የጤና ጉድለት ወይም የጉዳት ጡረታ አበል በመከፈል ላይ እያለ፣ ወይም

# PART EIGHT

# SURVIVORS PENSION AND GRATUITY

## 40. General

1/ Pension shall be paid to the survivors of a public servant who dies:

a) while receiving retirement or invalidity or incapacity pension; or

ለ) ቢያንስ ፲ ዓመት አገልግሎ በሥራ ላይ እያለ፤ ወይም

ሐ) በሥራ ላይ በደረሰበት ጉዳት ምክንያት ሕይወቱ ካለፈ ለተተኪዎቹ የጡረታ አበል ይከፈላል፡፡

፪/ ከ፲ ዓመት ያነሰ አገልግሎት ያለው የመንግሥት ሠራተኛ በሥራ ላይ እያለ ሕይወቱ ካለፈ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፫) ፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) ለተመለከቱት ተተኪዎች ዳረጎት ይከፈላቸዋል፡፡

፫/ የሟች ተተኪዎች የሚባሉት የሚከተሉት ይሆናሉ፡-

ሀ) ሚስት ወይም ባል፤

ለ) ከ፲፰ ዓመት ዕድሜ በታች የሆኑ ልጆች ወይም አካል ጉዳተኛ ወይም አዕምሮ በሽተኛ ልጅ ሲሆን ዕድሜው ከ፳፩ ዓመት በታች የሆነ፤

ሐ) ልጃቸው ሕይወቱ ከማለፉ በፊት ሙሉ በሙሉ ወይም በአብዛኛው በሟች ድጋፍ ይተዳደሩ የነበሩ ወላጆች፡፡

## ፵፩. የሟች ሚስት ወይም ባል ጡረታ አበል

፩/ ለሟች ሚስት ወይም ባል የሚከፈለው የጡረታ አበል ሟች ያገኝ ወይም ሊያገኝ ይችል የነበረው የጡረታ አበል ፶ በመቶ ይሆናል፡፡

፪/ የሟች ሚስት ወይም ባል የጡረታ አበል ተወስኖ በመቀበል ላይ እያለች ወይም እያለ ጋብቻ ከፈጸመች ወይም ከፈጸመ፡-

ሀ) ሚስት ዕድሜዋ ከ ፵፭ ዓመት በታች ከሆነ፤ ወይም

b) while in service upon completing at least 10 years of service; or

c) due to employment injury.

2/ If a public servant who has not completed 10 years of service dies while in service, his survivors falling under Sub-Article (3) paragraph (a) and (b) of this Article shall receive gratuity.

3/ The following shall be considered as survivors:

a) a widow or widower;

b) children of the deceased who are under the of age of 18 years or in the case of incapacitated child or a child with mental health problem, under the age of 21 years;

c) parents who were wholly or mainly supported by the deceased preceding his death.

## 41. Widow's or Widower's Pension

1/ The amount of pension payable to a widow or widower shall be 50 percent of the pension to which the deceased was or would have been entitled.

2/ Widow's or widower's pension shall be discontinued from the beginning of the month following remarriage where:

a) the age of the widow is less than 45 years; or

ለ) ባል ዕድሜው ከ፶ ዓመት በታች ከሆነ ጋብቻ ከተፈጸመበት ቀን ቀጥሎ ካለው ወር ጀምሮ በመከፈል ላይ ያለው የጡረታ አበል ይቋረጣል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፪) መሠረት መቋረጥ የሚገባውን የጡረታ አበል የተቀበለች ወይም የተቀበለ የሟች ሚስት ወይም ባል መልሶ የመክፈል ግዴታ አለባት ወይም አለበት፡፡

፬/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፪) እና (፫) ድንጋጌዎች በአካል ጉዳተኛ ሚስት ወይም ባል ላይ ተፈጻሚ አይሆኑም፡፡

፭/ ለሟች ሚስት ወይም ባል በዚህ አንቀጽ መሰረት ከአንድ በላይ የጡረታ አበል የሚከፈልበት ሁኔታ ሲያጋጥም አንዱና የሚበልጠው ብቻ ይከፈላል፡፡

## ፵፪. የሟች ልጅ ጡረታ አበል

፩/ ለሟች ልጅ የሚከፈለው የጡረታ አበል ሟች ያገኝ ወይም ሊያገኝ ይችል የነበረው የጡረታ አበል ፳ በመቶ ይሆናል፡፡

፪/ ሁለቱም ወላጆቹ ለሞቱበት ልጅ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) መሠረት የሚከፈለው የጡረታ አበል ፴ በመቶ ይሆናል፡፡

፫/ የጡረታ አበል የሚከፈላቸው ወይም ሊከፈላቸው ይችሉ የነበሩ ሁለቱም ወላጆቹ የሞቱበት ልጅ ከእያንዳንዳቸው አበል ፳ በመቶ ይከፈለዋል፡፡ ሆኖም የጡረታ አበሉ ድምር በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፪) መሠረት ሊከፈል ከሚችለው ያነሰ አይሆንም፡፡

b) the age of the widower is less than 50 years.

3/ A widow or widower shall return the pension received in violation of Sub-Article (2) of this Article.

4/ The provisions of Sub-Article (2) and (3) of this Article shall not be applicable to disabled widow or widower.

5/ Where a widow or widower is entitled to more than one pensions in accordance with the provisions of this Article, the one that is higher shall be paid.

## 42. Surviving Child's Pension

1/ The amount of pension payable to the surviving child shall be 20% of the pension to which the deceased was or would have been entitled.

2/ If both parents are dead, the amount of pension payable to the surviving child in accordance with Sub-Article (1) of this Article shall be 30%.

3/ If both parents of a child are dead, he shall receive 20% of the pension to which each of the deceased parent was or would have been entitled; provided, however, that the sum of such pensions shall not be less than the amount payable in accordance with Sub-Article (2) of this Article.

**፵፫. <u>የወላጆች ጡረታ አበል</u>**

ለሟች ወላጆች ለእያንዳንዳቸው የሚከፈለው የጡረታ አበል ሟች ያገኝ ወይም ሊያገኝ ይችል የነበረው የጡረታ አበል ፲፭ በመቶ ይሆናል፡፡ ሆኖም ከወላጆች ሌላ ተተኪ ከሌለ ፳ በመቶ ይሆናል፡፡

**፵፬. <u>የተተኪ ዳረጎት</u>**

ለማንኛውም ተተኪ የሚከፈለው ዳረጎት ለሟች በዚህ አዋጅ መሠረት ሊከፈለው ይገባ ከነበረው ዳረጎት እንደአግባቡ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፩ ንዑስ-አንቀጽ (፩) ወይም አንቀጽ ፵፪ በተወሰነው በመቶኛ ተባዝቶ ይታሰባል፡፡

**፵፭. <u>የተተኪዎች አበል ገደብ</u>**

፩/ በዚህ አዋጅ ከአንቀጽ ፵፩ እስከ አንቀጽ ፵፬ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ለተተኪዎች የሚከፈለው አበል ድምር ሟች ያገኝ ወይም ሊያገኝ ይችል ከነበረው አበል መቶ በመቶ ሊበልጥ አይችልም፡፡ ከተጠቀሰው መጠን በልጦ ከተገኘ ግን ከእያንዳንዱ ተተኪ አበል ላይ ተመጣጣኝ ቅናሽ ይደረጋል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) መሠረት የተተኪዎች ጡረታ አበል ከተስተካከለ በኋላ የተተኪዎች ብዛት ከቀነሰ የአበሉ መጠን እንደገና ይስተካከላል፡፡

**43. <u>Parent's Pension</u>**

The amount of pension payable to each parent shall be 15% of the pension to which the deceased was or would have been entitled. If there are no survivors other than the parents, the pension shall be 20%.

**44. <u>Survivors' Gratuity</u>**

The amount of gratuity payable to any survivor shall be the amount of gratuity to which the deceased would have been entitled and shall be calculated in accordance with the percentage specified in Article 41 Sub-Article (1) or Article 42 of this Proclamation, as the case may be.

**45. <u>Limits of Survivors' Benefits</u>**

1/ The total amount of benefits payable to survivors in accordance with Article 41 to Article 44 of this Proclamation shall not exceed 100% (Hundred percent) of the benefit to which the deceased was or would have been entitled. In the case of excess sum, each survivor's share shall be proportionately reduced until the total comes down to 100%.

2/ If the number of survivors is reduced subsequent to the adjustment made under Sub-Article (1) of this Article, further adjustment of the amount of benefits shall be made accordingly.

## ክፍል ዘጠኝ

## አበልን የሚመለከቱ የወል ድንጋጌዎች

### ፵፮. ስለዝቅተኛ የጡረታ አበል መጠንና የአበል መሻሻል

የአስተዳደሩ የሥራ አመራር ቦርድ ወቅታዊ የኑሮ ሁኔታንና የጡረታ ፈንዱን የመክፈል አቅም በማገናዘብ እስከ ፫ (ሶስት) ዓመት ባለ ጊዜ ውስጥ ዝቅተኛ ወርሃዊ የጡረታ አበል መጠንና የጡረታ አበል ማስተካከያ ያደርጋል፡፡

### ፵፯. የጡረታ አበል አከፋፈልና የመክፈያ ጊዜ

፩/ የጡረታ አበል የሚከፈለው በየወሩ ይሆናል፣

፪/ የአገልግሎት ጡረታ አበል መታሰብ የሚጀምረው የመንግሥት ሠራተኛው በዕድሜ ለጡረታ ብቁ ከሆነበት ቀጥሎ ካለው ወር መጀመሪያ ቀን አንስቶ ነው፣

፫/ የጤና ጉድለት ጡረታ አበል መታሰብ የሚጀምረው የመንግሥት ሠራተኛው በጤና ጉድለት ምክንያት መሥራት የማይችል መሆኑ በሕክምና ቦርድ ከተረጋገጠበት ቀጥሎ ካለው ወር የመጀመሪያ ቀን አንስቶ ነው፤

፬/ የጉዳት ጡረታ አበል መታሰብ የሚጀምረው የመንግሥት ሠራተኛው በጉዳት ምክንያት መስራት የማይችል መሆኑ በሕክምና ቦርድ ከተረጋገጠበት ቀጥሎ ካለው ወር የመጀመሪያ ቀን አንስቶ ነው፤

፭/ የተተኪዎች ጡረታ አበል መታሰብ የሚጀምረው ባለመብቱ ሕይወቱ ካለፈበት ቀጥሎ ካለው ወር መጀመሪያ ቀን አንስቶ ነው፤

## PART NINE

## GENERAL PROVISIONS RELATING TO BENEFITS

### 46. Minimum Pension and Pension Adjustment

The Administrations' Management Board, considering the existing living conditions and the ability to pay of the pension fund, shall adjust the minimum monthly pension and pension adjustment within 3 (three) years.

### 47. Mode and Period of Payment of Pension

1/ Payment of pension shall be effected monthly;

2/ Retirement pension shall commence to accrue as of the first day of the month following that in which the public servant retires;

3/ Invalidity pension shall commence to accrue as of the first day of the month following that in which the invalidity of the public servant is ascertained by medical board;

4/ Incapacity pension shall commence to accrue as of the first day of the month following that in which the permanent total incapacity sustained by the public servant is ascertained by medical board;

5/ Survivor's pension shall commence to accrue as of the first day of the month following that in which the beneficiary dies;

፮/ በዚህ አዋጅ ከተደነገገው የጡረታ መውጫ ዕድሜ በላይ በመንግሥት ሥራ ላይ ቆይቶ የሚቀርብ የጡረታ አበል ጥያቄ የጡረታ አበል ክፍያ መነሻ የሚታሰበው የመንግሥት ሠራተኛው ከመንግሥት ሥራ አቋርጦ የጡረታ አበል ክፍያ ጥያቄ ለአስተዳደሩ ካቀረበበት ቀጥሎ ካለው ወር የመጀመሪያ ቀን አንስቶ ይሆናል።

## ፵፰. <u>የዳረጎት አከፋፈልና የመክፈያ ጊዜ</u>

፩/ ማንኛውም ዳረጎት የሚከፈለው በአንድ ጊዜ ነው፡፡

፪/ የአገልግሎት ወይም የጤና ጉድለት ዳረጎት ተከፋይ የሚሆነው የመንግሥት ሠራተኛው ከሥራ ከተሰናበተበት ቀጥሎ ባለው ወር የመጀመሪያ ቀን ጀምሮ ነው፡፡

፫/ የጉዳት ዳረጎት ተከፋይ የሚሆነው የመንግሥት ሠራተኛው ላይ ጉዳት ስለመድረሱና መጠኑን የሚገልጽ ማስረጃ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ነው፡፡

## ፵፱. <u>የይርጋ ጊዜ</u>

፩/ ማንኛውም የውዝፍ አበል ወይም የዳረጎት ክፍያ ጥያቄ በአምስት ዓመት ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ ይታገዳል፡፡

፪/ የይርጋ ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው በመብቱ መጠቀም ከሚችልበት ቀጥሎ ካለው ቀን አንስቶ ነው፡፡

፫/ በሚከተሉት ምክንያቶች የባከነ ጊዜ ለይርጋ አቆጣጠር አይታሰብም፡-

ሀ) ባለመብትነቱን ለማረጋገጥ የተጀመረ የፍርድ ቤት ሥርዓት እስከሚጠናቀቅ የወሰደው ጊዜ፤

6/ If a public servant serve beyond retirement age provided in this Proclamation, the retirement pension payment shall commence after termination of service from public office and as of the first day of the month following that in which the retirement pension is requested to the Administration.

## 48. <u>Mode and Period of Payment of Gratuity</u>

1/ Payment of any gratuity shall be effected in lump sum at once.

2/ Retirement or invalidity gratuity shall be payable beginning with the first day of the month following that in which the public servant separates from the service.

3/ Incapacity gratuity shall be payable beginning with the day where evidence ascertaining the injury and its degree is submitted.

## 49. <u>Period of Limitation</u>

1/ Any claim for payment of arrears of pension benefit or payment of gratuity shall be barred by limitation after five years.

2/ The period of limitation shall begin to run from the day following that in which the right may be exercised.

3/ The period of limitation shall not include the following:

a) period lapsed due to a court process started to establish the right;

ለ) ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት መረጃ የማስተላለፍ ግዴታውን በወቅቱ ባለመወጣቱ ያለፈው ጊዜ፤

ሐ) ፈንዱ የቀረበለትን የክፍያ ጥያቄ መርምሮ ለመወሰን የወሰደው ጊዜ፡፡

## ፶. አበል የማግኘት መብትን ማስተላለፍ ስላለመቻሉ

አበል የማግኘት መብት የዕዳ መያዣ ሊደረግ ወይም በውርስም ሆነ በሌላ በማናቸውም ምክንያት ሊተላለፍ አይችልም፡፡

## ፶፩. ስለአበል በሕግ መከበር

በዚህ አዋጅ መሠረት የሚሰጥ አበል፦

፩/ ለመንግሥት ገቢ የሚሆን መቀጮ፤ ግብር ወይም ቀረጥ ለመክፈል፣ ወይም

፪/ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ቀለብ የመስጠት ግዴታን ለመወጣት በፍርድ ቤት ካልታዘዘ በስተቀር በሌላ ዕዳ ምክንያት አይከበርም፡፡

፫/ የማኅበራዊ ጤና መድህን አዋጅ ቁጥር ፮፻፺/፪ሺ፪ አንቀጽ ፱ እና የዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) እና (፪) ድንጋጌ ቢኖሩም ለማሕበራዊ ጤና መድህን የሚሰበሰብ መዋጮ በየወሩ ከጡረታ አበል ላይ ተቀንሶ ለማኅበራዊ ጤና መድህን ፈንድ ገቢ ይደረጋል፡፡ ሆኖም፦

ሀ) የጡረታ አበል በመቀበል ላይ ያለ ባለመብት በሠራተኛነት በመቀጠር ደመወዝ የሚያገኝ ከሆነ የጤና መድህን መዋጮ የሚቀነሰው በየወሩ ከሚከፈለው ደመወዝ ላይ ብቻ ነው፤

b) period lapsed due to non fulfillment by the public office of its obligation to submit evidentiary documents on time;

c) period necessary for the decision of benefit entitlement by the Fund.

## 50. Non-Transferability of Entitlement to Benefits

The right to receive benefits shall not be pledged or transferred by inheritance or any other means.

## 51. Attachment of Benefits by Law

Benefits payable in accordance with this Proclamation shall not be attached in relations to any debts unless ordered by a court in respect of:

1/ public fines, taxes or charges; or

2/ fulfillment of the obligation to supply maintenance orderd by the court in accordance with the relevant law.

3/ Notwithstanding the provision of Article 9 of Social Health Insurance Proclamation No. 690/2010 and Sub Article (1) and (2) of this Article, a contribution for social health insurance shall be deducted monthly from pension benefit and transferred to social health insurance fund. However:

a) if the beneficiary who receives monthly pension benefit also receives salary from employment, a contribution for social health insurance shall be deducted only from his monthly salary;

ለ) የጡረታ አበል በመቀበል ላይ ያለ ባለመብት የተተኪም ጡረታ አበል የሚያገኝ ከሆነ የጤና መድህን መዋጮ የሚቀነሰው በራሱ ከሚያገኘው የጡረታ አበል ብቻ ነው፡፡

## ክፍል አሥር

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፶፪. የመብቶች ግንኙነት

፩/ የጡረታ አበል በመቀበል ላይ ያለ ባለመብት በመንግሥት መሥሪያ ቤት ከተቀጠረና በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፰ ንዑስ-አንቀጽ (፩) ፊደል-ተራ (ሐ) የተደነገገው ጡረታ መውጫ ዕድሜ ያልደረሰ ከሆነ አዲሱ አገልግሎት ከቀድሞ አገልግሎቱ ጋር ተደምሮ ይታሰብለታል፡፡ ሆኖም የአገልግሎት የጡረታ አበል በመቀበል ላይ ያለ ባለመብት እንደገና በመቀጠር የፈጸመው አገልግሎት ተደምሮና ተሻሽሎ አበል የሚከፈለው የሠራተኛው ዕድሜ ፷ ዓመት ከሚሞላበት ቀጥሎ ካለው ወር መጀመሪያ ቀን አንስቶ ይሆናል፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ እንደገና የታሰበው አበል ከቀድሞው አበል ያነሰ ከሆነ የቀድሞውን አበል የማግኘት መብት ይኖረዋል፡፡ ሆኖም ወደ ሥራ በመመለስ ለተፈጸመ አገልግሎት የሚከፈል አበል ወይም የጡረታ መዋጮ ተመላሽ አይኖርም፡፡

b) if the beneficiary who receives pension benefit also receives survivors' pension benefit, the contribution for social health insurance shall be deducted only from the pension benefit he gets by his own.

## PART TEN

## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 52. Relationship between Entitlements

1/ If a beneficiary who receives retirement benefit is employed by a public office and has not reached the retirement age stipulated under Sub-Article (1) paragraph (c) of Article 18 of this Proclamation, his new service year shall be added to his previous service; however, for the retirement beneficiary the new service shall be added only when he attains the retirement age of 60.

2/ Without prejudice to Sub-Article (l) of this Article, if the amount of retirement pension calculated based on the accumulated service is less than the previous one, the beneficiary shall have the right to receive the previous pension benefit; however, there shall not be any payment of benefit or contribution reimbursement for the service rendered by the public servant.

፫/ በዚህ አዋጅ ክፍል ስምንት የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ ባለመብት በዚህ አዋጅ መሠረት ከአንድ በላይ የጡረታ አበል የሚያገኝበት ሁኔታ ሲያጋጥም ሊከፈል የሚገባው የአበል መጠን አስተዳደሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይወሰናል፡፡

፬/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፮ ንዑስ-አንቀጽ (፪) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ከግል ወደ መንግሥት ይዞታ በተዛወረ ድርጅት ድርጅቱ ከመዛወሩ በፊት ሲከፈል የነበረ ወርሃዊ የጡረታ አበል በዚህ አዋጅ መሰረት ተስተካክሎ ይከፈላል፡፡

፭/ ከ፲ ዓመት ያላነሰ አገልግሎት ላላቸው ወይም ከአምስት ዓመት ያነሰ አገልግሎት ኖሯቸው አገልግሎታቸው ሲቋረጥ የጡረታ መውጫ ዕድሜ ላይ ለደረሱ ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊዎችና የምክር ቤት አባላት አበል አወሳሰን የመከላከያ ሠራዊት ወይም የፖሊስ አባል ያልሆኑ የመንግሥት ሠራተኞችን የሚመለከቱ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች እንደአግባቡ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

፮/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፬) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በአዋጅ ቁጥር ፮፻፶፫/፪ሺ፩ አንቀጽ ፶፭ መሰረት መብቶችና ጥቅሞቹ እንዲቋረጡ የተወሰነበት ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊ ወይም የምክር ቤት አባል በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፱(፭) ወይም አንቀፅ ፳፫(፪) መሰረት የሚከፈለው የጡረታ አበል ይቋረጣል፡፡

3/ Without prejudice to the provisions of Part Eight of this Proclamation, if a beneficiary is entitled to more than one benefits, in accordance with this Proclamation the amount of benefit to be paid shall be determined in accordance with the Directive to be issued by the Administration.

4/ Without prejudice to Sub-Article (2) of Article 16 of this Proclamation, a retired employee of a nationalized enterprise who is receiving monthly benefit on the date of nationalization shall continue to get the amount of pension benefit adjusted in accordance with this Proclamation.

5/ Senior government officials and members of parliament who have completed at least 10 years of service or who attains the age of retirement upon separating from service before completing five years of service shall be entitled to benefits applicable to public servants other than members of the defense force and the police in accordance with the provisions of this Proclamation.

6/ Without prejudice to the provision of Sub-Article (4) of this Article, the payment of pension benefit to an outgoing senior government official or member of parliament pursuant to Article 19(5) or Article 23(2) of this Proclamation shall be terminated following a decision to terminate his rights and benefits in accordance with Article 55 of Proclamation No. 653/2009.

፯/ ይህ አዋጅ ከሚጸናበት ቀን አንስቶ ወደ ፊት ዕድሜው ፷ ዓመት ከመሙላቱ በፊት በራስ ፍቃድ የአገልግሎት የጡረታ አበል መቀበል የጀመረ የመንግሥት ሠራተኛ በዚያው የመንግስት መሥሪያ ቤት (ድርጅት) ከተቀጠረ ይከፈል የነበረው የጡረታ አበል ይቋረጣል፡፡

## ፶፫. <u>መረጃ የመስጠትና የመተባበር ግዴታ</u>

፩/ ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት በዚህ አዋጅ ክፍል ሁለት ድንጋጌዎች መሠረት ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም የሚያስፈልጉ እያንዳንዱን የመንግሥት ሠራተኛ የሚመለከቱ መረጃዎችና ማስረጃዎች ማሰባሰብ፣ ማጠናቀር፣ ማደራጀትና በአስተዳደሩ በሚወሰነው ጊዜና ቅጽ መሠረት ለአስተዳደሩ የማስተላለፍ ግዴታ አለበት፡፡

፪/ ይህን አዋጅ በሥራ ላይ ለማዋል እንዲቻል ማንኛውም ሰው የጽሁፍ ማስረጃ እንዲልክ ወይም ቀርቦ አስተያየትና መረጃ እንዲሰጥ በአስተዳደሩ ሲጠየቅ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

፫/ የሚመለከታቸው አካላት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፪ ንዑስ-አንቀጽ (፭) በሚሰጥ ውክልና መሠረት የጡረታ መዋጮ በመሰብሰብ ረገድ ከአስተዳደሩ ጋር የመተባበር ግዴታ ይኖርባቸዋል፡፡

7/ If a public servant who separate from service by voluntary resignation before he attains the age of 60 and begins receiving benefit is reemployed in the same public office from which he is retired as of the effective date of this proclamation the payment of benefit shall be terminated.

## 53. <u>Obligation to Provide Evidentiary Data and Duty to Cooperate</u>

1/ Any public office shall collect, compile and submit to the Administration, in accordance with the provisions of Part Two of this Proclamation and in accordance with the form and within the time limit specified by the Administration, evidentiary data relating to each public servant which are necessary for the implementation of this Proclamation.

2/ For the purpose of implementing this Proclamation, any person shall provide information or written evidence or appear and testify or give his opinion when so requested by the Administration.

3/ The appropriate bodies shall have the duty to cooperate with the Administration in collecting pension contributions pursuant to delegations of powers under Article 12 Sub-Article (5) of this Proclamation.

**፶፬. <u>የአስተዳደሩ ውሳኔዎች</u>**

፩/ በዚህ አዋጅ መሰረት ለሚሰጥ ለማናቸውም ዓይነት አበል ብቁ የሚያደርጉ ሁኔታዎች መሟላታቸው የሚረጋገጠውና የአበሉ ዓይነትና መጠን የሚወሰነው በአስተዳደሩ ይሆናል፡፡

፪/ አስተዳደሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ውሳኔ የሚሰጠው የራሱን የመረጃ ማህደር፣ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፫ መሠረት የሚተላለፉትን መረጃዎችና እንደ አግባቡ ባለመብቱ የሚያቀርባቸውን ተጨማሪ ማስረጃዎች መሠረት በማድረግ ይሆናል፡፡

፫/ በአስተዳደሩ የመረጃ ማህደርና በቀረበለት ማስረጃ መካከል ልዩነት ቢፈጠር ተቀባይነት የሚኖረው ማስረጃ በአስተዳደሩ ይወሰናል፡፡

**፶፭. <u>ውሳኔን እንደገና ስለመመርመር</u>**

፩/ ቅሬታ ያለው ባለመብት በሚያቀርበው ጥያቄ ወይም በራሱ አነሳሽነት አስተዳደሩ ቀደም ብሎ የሰጠውን ውሳኔ እንደገና ለመመርመር ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፩ የተደነገገው ቢኖርም አስተዳደሩ ውሳኔውን እንደገና ሲመረምር የአበል መሰረዝ፣ መቀነስ ወይም መቋረጥ ሊያስከትል የሚችል በቂ ምክንያት ያገኘ እንደሆነ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ ሊሰረዝ፣ ሊቀነስ ወይም ሊቋረጥ በሚገባው አበል መጠን ክፍያው ታግዶ እንዲቆይ ማድረግ ይችላል፡፡

**54. <u>Decision of the Administration</u>**

1/ The fulfillment of conditions for entitlement to any kind of benefit payable in accordance with this Proclamation and the amount of the benefit shall be decided by the Administration.

2/ The decision of the Fund to be rendered in accordance with Sub-Article (1) of this Article shall be based on its own records, evidentiary data submitted to it in accordance with Article 53 of this Proclamation and, as may be appropriate, on additional evidences produced by the beneficiary.

3/ In the case of a difference between the records of the Administration and evidentiary data submitted to it, the prevailing evidence shall be decided by the Administration.

**55. <u>Review of Decisions</u>**

1/ The Administration may review its previous decision upon request by an aggrieved beneficiary or on its own initiative.

2/ Notwithstanding the provisions of Article 51 of this Proclamation, where upon review the Administration finds that there is reasonable ground for cancellation, deduction or termination of benefits, it may suspend payment to the extent the benefit is to be cancelled, deducted or terminated.

፫/ የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፩ ድንጋጌ ቢኖርም እንደገና በተደረገ ምርመራ የጡረታ አበል እንዲቀነስ አስተዳደሩ ከወሰነ ወይም ከዚህ አዋጅ ድንጋጌ ውጪ ያለአግባብ የጡረታ አበል ከተከፈለ አስተዳደሩ ከባለመብቱ አበል ላይ እየቀነሰ ለጡረታ ፈንዱ ገቢ የማድረግ ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

3/ Notwithstanding the provisions of Article 51 of this Proclamation, if the Administration, upon review, has decided to deduct the benefit or the benefit paid is contrary to this Proclamation, it shall have the power to deduct the amount paid thereof from the benefit of the beneficiary and transfer same to pension fund.

## ፶፮. ስለ ይግባኝ

፩/ አስተዳደሩ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፬ ወይም አንቀጽ ፶፭ መሠረት በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ባለመብት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፯ ለተቋቋመው የማሕበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ የማቅረብ መብት ይኖረዋል፡፡

፪/ የይግባኝ አቤቱታ ለጉባዔው መቅረብ የሚችለው ይግባኝ በሚባልበት ጉዳይ ላይ ውሳኔ በተሰጠ እስከ አንድ ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ ነው፡፡

፫/ ጉባዔው የቀረበለትን የይግባኝ አቤቱታ ከዚህ አዋጅ ድንጋጌዎችና አዋጁን ለማስፈጸም ከወጡ ደንቦችና መመሪያዎች አንፃር መርምሮ የአስተዳደሩን ውሳኔ መለወጥ፣ ማሻሻል ወይም ማጽናት ይችላል፡፡

፬/ ጉባዔው በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፫) መሠረት የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡ ሆኖም የጉባዔው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለው ብሎ የሚያምን ተከራካሪ ወገን ውሳኔው በተሰጠ በ፴ ቀናት ውስጥ ይግባኙን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የማቅረብ መብት ይኖረዋል፡፡

## 56. Appeal

1/ A beneficiary who is aggrieved by the decision of the Administration made pursuant to Article 54 or Article 55 of this Proclamation shall have a right to lodge an appeal to the Social Security Appeal Tribunal established under Article 57 of this Proclamation.

2/ An appeal may lodged to the Tribunal within one year from the date of the decision which is subject to the appeal.

3/ The Tribunal, upon examining an appeal submitted to it in line with the provisions of this Proclamation and Regulations and Directives issued for the implementation of this Proclamation, may reverse, vary or confirm the decision of the Administration.

4/ The decision of the Tribunal given in accordance with Sub-Article (3) of this Article shall be final; provided, however, that any party may appeal to the Federal Supreme Court within 30 days, if there is a fundamental error of law in the decision.

## ፶፯. <u>የማኅበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ</u>

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፮ መሠረት የሚቀርቡ ይግባኞችን እየመረመረ ውሳኔ የሚሰጥ የማሕበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

፪/ የጉባዔው አደረጃጀትና የአባላት አሰያየም በብሔራዊ ባንክ አቅራቢነት በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሰየሙ ይሆናል፡፡

፫/ ከጉባዔው አባላት አብዛኞቹ በጉባዔው ስብሰባ ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፡፡

፬/ የጉባዔው ውሳኔ የሚተላለፈው በስብሰባው በተገኙ አባላት በአብላጫው ድምጽ ሲደገፍ ነው፤ ሆኖም ድምጽ እኩል ለእኩል ከተከፈለ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፡፡

፭/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ጉባዔው የራሱን የአሠራር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ፶፰. <u>ከግብር ነፃ ስለመሆን</u>

በዚህ አዋጅ መሰረት በሚከፈል የጡረታ አበል፣ በሚሰበሰብ የጡረታ መዋጮ እና ከጡረታ ፈንድ ኢንቨስትመንት በሚገኝ ትርፍ ላይ ግብር አይከፈልም፡፡

## ፶፱. <u>የመረጃ አያያዝ ኃላፊነት</u>

አስተዳደሩ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚቀርቡለትን መረጃዎች የመሰብሰብና በዘመናዊ (ዲጂታላይዝድ በሆነ) የመረጃ አያያዝ ዘዴዎችን በመጠቀም አደራጅቶ የመያዝ ኃላፊነት አለበት፡፡

## 57. <u>Social Security Appeal Tribunal</u>

1/ A Social Security Appeal Tribunal is hereby established to hear and decide on appeals to be submitted in accordance with Article 56 of this Proclamation.

2/ The organization and assignment of members of the Tribunal shall be nominated by the National Bank and appointed by the Prime Minister.

3/ There shall be quorum where more than half of the members of the Tribunal are present at its meeting.

4/ The Tribunal shall pass decisions by majority vote; provided, however, that the Chairperson shall have a casting vote in case of a tie.

5/ Without prejudice to the provisions of this Article, the Tribunal may issue its own directive of procedures.

## 58. <u>Tax Exemption</u>

No tax shall be payable on benefits received, pension contributions collected and profits earned from investment of pension funds, in accordance with this Proclamation.

## 59. <u>Responsibility of Data Keeping</u>

The Administration shall be responsible for data collection and digitization of data registration in accordance with this Proclamation.

## ፷. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

፩/ ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት ለተፈጠሩ ሕጋዊ ሁኔታዎች ቀደም ሲል ሲሰራባቸው የነበሩ ሕጎችና መመሪያዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

፪/ አስተዳደሩ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴ የተጠቀሰውን የአካል ጉዳት መወሰኛ ሠንጠረዥ እስከሚያወጣ ድረስ የሕክምና ቦርዶች የሚከተሉት አሰራር ተፈጻሚነቱ ይቀጥላል፡፡

፫/ የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፯ ንዑስ-አንቀጽ (፭) እንደተጠበቀ ሆኖ ከሰኔ ፩ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም በፊት በመንግስት መሥሪያ ቤት፣ በመንግሥት የልማት ድርጅት እና በመንግስት በሚካሄድ ፕሮጀክት ወይም ፕሮግራም ለተወሰነ ጊዜ ያገለገለ ሠራተኛ ከሐምሌ ፩ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም ጀምሮ ይህ አዋጅ በሚጸናበት ቀን በሥራ ላይ ለሚገኝና ተገቢውን የጡረታ መዋጮ ለከፈለ ሠራተኛ የዚህ አዋጅ ድንጋጌ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

፬/ የአዋጁ አንቀጽ ፲፱ ንዑስ-አንቀጽ (፬) እና አንቀጽ ፶፱ ንዑስ-አንቀጽ (፩) ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ከሐምሌ ፩ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም በፊት ቢያንስ ፳፭ ዓመት አገልግሎ በተለያየ ምክንያት ሥራውን ላቋረጠ ሠራተኛ የአዋጁ አንቀጽ ፲፱ ንዑስ-አንቀጽ (፫) ድንጋጌ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## 60. Transitory Provisions

1/ Previous laws and Directives shall remain applicable to legal situations created before the coming into force of this Proclamation.

2/ Until the Administration issues the schedule referred to in Article 30 of this Proclamation to determine the degrees of incapacity, the practices followed by medical boards shall remain applicable.

3/ Without prejudice to Sub-Article (5) of Article 17 of this Proclamation, the provisions of this Proclamation shall apply to public servant who have been employed in definit period of time in a public office, public enterprise or project or program carried out by government before June 08, 2003 and become permanent; provided,, however, that from July 08, 2015 he shall be serving as public servant on the date of coming into force of this Proclamation and pays the due contribution.

4/ Without prejudice to Sub-Article (4) of Article 19 and Sub-Article (1) of Article 59 of this Proclamation, Sub-Article (3) of Article 19 of this Proclamation shall be applicable to public servant who have completed at least 25 years of service and separates from service on different grounds before July 08, 2015.

፭/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም ቀደም ሲል የመንግሥት ሠራተኛ ወይም የጡረታ አበል ተጠቃሚ ባለመብት ሆኖ በወንጀል ጥፋት ምክንያት ከሦስት ዓመት ያላነሰ ጽኑ እስራት ቅጣት ተፈርዶበት የዘለቄታ የጡረታ መብቱን ያጣ ባለመብት ከሐምሌ ፩ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም አንስቶ ውዝፍ አበል ሳይጨምር ለወደፊት የጡረታ አበል የማግኘት መብት ይኖረዋል፡፡

፮/ ከሐምሌ ፩ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም ጀምሮ በሥራ ላይ ለሚገኝ ወይም በኋላ ለሚቀጠር የመንግሥት ሠራተኛ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፭) በተገለጸ ምክንያት ያልተያዘለት አገልግሎት ለወደፊት ከአዲሱ አገልግሎቱ ጋር ተደምሮ እንዲያዝለት ይደረጋል፡፡

## ፷፩. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

፪/ አስተዳደሩ ይህን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) መሠረት የሚወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ፷፪. ቅጣት

የያዘውን ማስረጃ በዚህ አዋጅ መሠረት ለመስጠት ፈቃደኛ ያልሆነ ወይም የዚህን አዋጅ እና ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጡ ደንብ እና መመሪያዎች ድንጋጌ አፈፃፀም የሚያሰናክል ተግባር የፈጸመ ማንኛውም ሰው በወንጀል ሕግ ተጠያቂ ይሆናል ፡፡

5/ Without prejudice to Sub-Article (1) of this Article, a public servant or beneficiary who lost his right to have retirement pension benefit due to criminal punishment for not less than three years rigorous imprisonment, shall have right to effective date of July 08, 2015; provided, however, he cannot claim arrear payments.

6/ A period of service not counted for the reason mentioned in Sub-Article (5) of this Article shall be added to the new services of the public' servant who is engaged on or after the effective date of July 08,2015.

## 61. Power to Issue Regulation and Directive

1/ The Council of Ministers may issue Regulations necessary for the implementation of this Proclamation.

2/ The Administration may issue Directives necessary for the implementation of this Proclamation and Regulations issued pursuant to Sub-Article (1) of this Article.

## 62. Penalty

Any person who refuses to provide evidence under this Proclamation or who commits an act that interferes with the implementation of this Proclamation shall be liable under Criminal Law.

**፷፫. <u>የተሻሩና ተፈጻሚ የማይሆኑ ሕጎች</u>**

፩/ የሚከተሉት በዚህ አዋጅ ተሽረዋል፡-

ሀ) የመንግሥት ሠራተኞች የጡረታ አዋጅ ቁጥር ፯፻፲፬/፪ሺ፫ (በአዋጅ ቁጥር ፱፻፯/፪ሺ፯ እንደተሻሻለ)፤

ለ) የመንግሥት ልማት ድርጅቶችን ወደ ግል ለማዛወር የወጣው አዋጅ ቁጥር ፩፻፵፮/፲፱፻፺፩ አንቀጽ ፲፪ እና የጡረታ ሽፋንን የሚመለከተው የአንቀጽ ፴ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ፤

ሐ) ከኃላፊነት የተነሱ የሀገርና የመንግሥት መሪዎች፣ ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊዎች የምክር ቤት አባላትና ዳኞች መብትና ጥቅሞች አዋጅ ቁጥር ፮፻፶፫/፪ሺ፩ አንቀጽ ፲፪ እና አንቀጽ ፳፩፤

፪/ ይህን አዋጅ የሚቃረኑ ማናቸውም ሕጎች ወይም የአሠራር ልምዶች ይህን አዋጅ በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆኑም፡፡

**፷፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ መጋቢት ፱ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም**

**ሣህለ ወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**63. <u>Repealed and Inapplicable Laws</u>**

1/ The following are hereby repealed:

a) The Public Servants Pension Proclamation No. 714/2011 (as amended by Proclamation No. 907/2015);

b) Article 12 and with respect to pension coverage, the provision of Sub-Article (1) of Article 30 of the Privatization of Public Enterprises Proclamation No. 146/1998;

c) Article 12 and Article 21 of the Outgoing Heads of State and Government, Senior Government Officials, Members of Parliament and Judges Proclamation No. 653/2009.

2/ No laws or customary practices shall, in so far as they are inconsistent with this Proclamation, shall have force and effect in respect of matters provided for by this Proclamation.

**64. <u>Effective Date</u>.**

This Proclamation shall enter into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, On this 18th Day of March, 2022.**

**SAHLE-WORK ZEWDE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**